# ምዕራፍ ፲፬

# እንደገና ወደ ራስ መመለስ

በጌዴኦ፣ በሻሸን፣ በኡዮራ፣ በማረቆ እየተዘዋወረ ያገለገለው እና እግዚአብሔር ስለ ስሙ ያሳዩትን ፍቅር የማይረሳ አምላክ እንደሆነ የተረዳው ኬዳሞ በማረቆ የነጣውን አዝመራ እያየ በሚተጋበት ወቅት አገልግሎቱን አቁሞ እንዲመለስ የሚያደርገው ሁኔታ ገጥሞት ነበር። በእርግጥ የመመለሱ ዋና ምክንያት በቤተ ክርስቲያን በራሷ የቀረበ "የተመለስ" ጥያቄ ቢሆንም ኬዳሞም በልቡ የራሱን መላ ዘይዶ ነበር። በማረቆ የመጨረሻ ቆይታው አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ባደረገበት ተጽእኖ ለስድስት ወራት ያለ ደመወዝ መኖሩ ይታወሳል። በዚህ ሁኔታ ያዘነው ኬዳሞም ያረጁ እናቱን እንዲረዳ እና ሁኔታዎችን እንዲያስተካክል በተመለሰበት የኑሮ አቅጣጫውንም በዚያው ሊያጸና ወሰነ። እግዚአብሔር ስለ እኔ እና ስለ ቤተሰቤ ያስባል ከሚለው የተስፋ ቃል ተላቅቆ ኑሮውን ሊያመቻች ወደደ። እናም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ትውልድ አገሩ እና ወደ ራሱ ኑሮ ተመለሰ።

በዚህ ጊዜ ወንጌላዊው ከእግዚአብሔር ሃሳብ ተቃርኖ መንፈሳዊ ነገሩ አልደነዘዘም። ነገር ግን እንደ ከዚህ ቀደሞቹም ሆነ የኋለኛው የሕይወት ውሳኔዎቹ በብዙ ጸሎት እና የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ የወሰነው አልነበረም።

ኬዳሞ ሻሸን ከተመለሰ በኋላ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሙሉ ጊዜውን በወንጌል አገልግሎት ከማሳለፍ ግማሽ  ጊዜውን የራሱን ኑሮ እና የቤተሰቡን ሕይወት የሚያስተካክልበት እንዲሆን አቀደ። ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያንን ድጎማ እና የመሪዎችን ቀና ውሳኔ በመጠባበቅ ራሱን ላለመጉዳትም ወጥኖ ተወልዶ ያደገበትን ግብርና ያቀላጥፍ ጀመር። ጎን ለጎንም በሳምንት ለአራት ቀናት ያህል ወንጌልን እየሰበከ ያመኑትን ቃሉን እያስተማረ፣ ቤተ ክርስቲያንን እያገለገለ ማሳለፍም ጀመረ። ይህ በኬዳሞ ሕይወት የተከሰተ ከጥሪው ያፈነገጠ እና ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ ሰጥቶ አልረካ ሲል ራሱን ያስረከበባትን ቃል ኪዳን ያልጠበቀ አጋጣሚ እንደ ሁለተኛው የሕይወቱ የሽንፈት ጉዞ ሊቆጠር ይችላል።

ምናልባትም ይህ የራሱን እና የቤተሰቡን ኑሮ እያሸነፈ ለማገልገል የወሰነው ውሳኔ እግዚአብሔር ከቆይታ በኋላ ባይልክ ኖሮ ኬዳሞን ለብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያንና ሌሎች ሕዝቦች ብሎም በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጪ ተዘዋውሮ የሚያገለግል ታላቅ

*አገልጋይ መሆኑ እንዲቀር ሊያደርግ ይችል ነበር። ይልቁንም በሻሾን እልፍ ሲልም በከምባታ እና ሃዲያ አውራጃ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አገልጋይ ብቻ ሊያደርገው ይችል ነበር። ታሪኩን ከባለታሪኩ ለመስማት ወደ ወንጌላዊው ትረካ እንመለስ።*

---------------------//---------------------

## ገበሬው ወንጌላዊ

ቤተ ክርስቲያን የቤተሰቤን ሁኔታ አይታ ስትጠራኝና እኔ ደግሞ በማረቀ የነበረኝን ፍሬያማ አገልግሎት ላይ ሁኔታው ጥያቄ የሚፈጥር ነበር። ከምንም በላይ ሁኔታውን ለኔ ከባድ ያደረገው ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ልካኝ ቤተሰቤን እና ጓዜን ጠቅልዬ አገልግሎት ላይ ሆኜ ለስድስት ወራት ቤተ ክርስቲያን የምትልከው 20 ብር የቀለብ ድጎማ ከሽማግሌዎች መካከል አንዱ በኔ ላይ ቅሬታ ስለነበረ ብቻ መቆሙ ነበር። እኔ ይህንን ሁኔታ አገልግሎቱ እንዲቆም ሰይጣን የተጠቀመበት ስልት ነው ብዬ ከባለቤቴ ጋር ብዙ ዋጋ እየከፈልን ማገልገል ቀጥለን የነበረ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን ወደ ቤት እንድመለስ እና እናቴንም እንድጦር ስትጠራኝ ግን ከዚህ በኋላ በፍጹም የሰውን እጅ ላለማየት ወስኜ ነበር የተመለስኩት።

ወደ ሻሾን እንደተመለስኩም የተበላሸውን ንብረት አስተካክዬ ወዲያውኑ ወደ እርሻ ሥራዬ ገባሁ። ራሴን ለወንጌል ከመለየቴ በፊት ብርቱ ገበሬ አድርጎ ያሳደገኝ ቆፍጣናው አባቴ ምስጋና ይግባውና ጥሩ ገበሬ ስለነበርኩም ግብርናው ለኔ በጣም ቀላል ነበር። በጊዜው ያልተገሩ ነገር ግን በደንብ ደልበው ለእርሻ የደረሱ ሦስት በሬዎች ስለነበሩኝ እነርሱን ገርቼ የእናቴንም የራሴንም እርሻ ጥሩ አድርጌ አረስኩ።

በ1955 ዓ.ም በወርኃ ጥር እርሻዬን አርሼ በዓመቱ መጨረሻ ጥሩ ምርት ለማግኘት ተዘጋጀሁ። በዚሁ ጊዜ እኔ ግብርናውን እንዲህ ባስኬድም ቤተ ክርስቲያንም ከዚህ ቀደም የምትከፍለኝን አልቀበልም ብዬ በሻሾን ዙሪያ እና በሌሎች ልዩ ልዩ ቦታዎች በከምባታ የተለያዩ ወረዳዎች ሳይቀር የአገልግሎት ጥሪ እየተደረገልኝ እየሄድኩ አገለግላለሁ። በአካባቢዬም ከሥራ በሚተርፈው ሰዓት ወንጌልን እየሰበክሁ እውላለሁ።

በዚህ መልኩ የጀመርኩት ሥራ እና ያለኝ አገልግሎት እንዳይበደልም ሰኞ፣ ማክሰኞ እና ሐሙስን ሙሉ ለሙሉ በሥራ ሳላልፍ ረቡዕ፣ አርብ፣ ቅዳሜና እሁድን ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መድቤ ወንጌል በመስበክ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና ምእመናንን በማስተማር አገልግሎቴን ቀጠልኩ።

የግብርና ሥራዬም ውጤታማ ሆኖ በ1955 ዓ.ም ብቻ የራሴን፣ የእናቴን እና የሌላ ሰው እርሻ ወስጄ በዘመኑ ለእኩል በሚባለው ዓይነት (ከባለቤቱ ጋር የሚገኘውን ትርፍ ለመካፈል) ሠርቼ በጣም ብዙ የእህል ምርት ማፈስ ቻልን። ከአንድ ቦታ ብቻ ያገኘሁትን 12 ኩንታል እህል ሸጬም አንድ ጊደር እና አንድ ወይፈን ገዛሁ።

ኑሮአችንም በብዙ መልኩ ተመቻቸ። ልክ እንደ ባላባት ለባለቤቴ በቅሎ እና ለኔ ፈረስ ነበረን።

ግብርናውም እየተስፋፋ ሄዶ ሁለት ጥማድ በሬዎች ገዛቼ አንዱን በሬ የሌለው ገበሬ ሁለት ቀን የኔን አንድ ቀን የራሱን ሊያርስ ተስማምተን በዚህ ዓይነት አሳረስኩ። የኔ ቤተሰብም ሆነ የእናቴ ማረቆ እያለን የተቸገርነው ተረስቶ ኑሮአችን በደንብ የተስተካከለ በመሆኑ ቅቤ እና ወተት እንደልባችን ነበረን።

በዚሁ ጊዜ ከራሴ የግል ምቾት ባሻገር በቤተ ክርስቲያን አክብሮት ተሰጥቶኝ በብዙ ጉዳዮች ላይ ምክር እሰጥ ነበር። በተለያዩ ቦታዎች እየዞርኩም በደንብ አገለግል ነበርና በመንፈሳዊ አገልግሎት በኩልም ተመችቶኝ ነበር። ከዚህም ሌላ እናቴን ጨምሮ ሌሎች ዘመዶቼን ሳልለያቸው በቅርብ አብሬ እየኖርኩ በብዙ መልኩ እረዳቸው ነበር። ለእኔም ተወልጄ ባደግኩበት ተሯሩጬ በተጫወትኩበት እና ከብቶች ባገድኩበት ምድር ላይ መኖር አስደሳች ነበር።

በዚሁ ጊዜ የባለቤቴ የእንጀራ አባት የመሬት ክርክር ገጥሟቸው እኔ እንድከራከርላቸው ወክለውኝ ነበር። በዚህ መልኩም ማኅበራዊ ግዴታዎቼን ሁሉ እየተወጣሁ ተመችቶኝ እኖር ነበር። ቤተ ክርስቲያኔን ሳገለግል እና ሳማክር በነበረበት ጊዜም እግዚአብሔር እንደገና ለዚያ ምድር ታሪክ መለወጥ ምክንያት የሚሆን ነገር በውስጤ አስቀመጠ።

## ለሻሾን ምድር እንደገና የእውቀት ብርሃን መፈንጠቅ

የባለቤቴ የእንጀራ አባት ለመሬት ክርክር ወክለውኝ ሆሳዕና የአውራጃ ዳኛ መሬታቸው እንዲወሰድባቸው የፈረደውን ፍርድ ለማስቀየር ወደ አዲስ አበባ ይግባኝ ለማለት መጥቼ ነበር። ምንም እንኳን የሄድኩበት ጉዳይ ተሳክቶ ለባለቤቴ የእንጀራ አባት የምስራች ለማብሰር ባልታደልም እግዚአብሔር ግን በሻሾን ምድር የተንሰራፋውን የመኃይምነት ጨለማ የሚገፍ ምክር አስጨብጦኝ ነበር የተመለስኩት። በዚያ ዘመን የቀድሞ የከምባታና ሃዲያ ባላባቶችና መልከኞች ሕዝቡን እንደፈለጉ ረግጠው ለመግዛት እንዲመቻቸው የሕዝቡን መማር አይፈልጉም ነበርና ሻሾንም ትምህርት ቤት እየከፈትን ሕዝቡን እንዳናስተምር ከልክለውን ነበር።

እኔም ይህንን አይቼ በጣም አዝን እና ይሰማኝ ነበር። ያኔ ባለቤቴ ብዙነሽን እያስታመምኩ ሻሾን በነበርንበት ጊዜ እንደከፈትነው አይነት ትምህርት ቤት መክፈት ባለመቻላችን ሕጻናቱ እና ወጣቱ ዝም ብለው ሜዳ ላይ ፈስሰው እረኛ እና አራሽ ሆነው ይውሉ ነበር። በዚህ ጊዜ ነበር ለጠቀስኩት የመሬት ክርክር ወደ አዲስ አበባ ያቀናሁት። አዲስ አበባም የእኛን አካባቢ ወክለው የፓርላማ አባል በሆኑት ቀኛዝማች ስዩም ቤት አድር ነበር። ቀኛዝማች ስዩም ገና ለምርጫ በሚወዳደሩበት ጊዜ ምርጫውን እንድታስተባብር ቤተ ክርስቲያንን ጠይቀው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ እኔን ወክላኝ ሳስተባብር ስለነበር ጥሩ ትውውቅ ነበረን። እኔም ቀኛዝማች ስዩም የአካባቢውን

ሕዝብ ወክለው ፓርላማ የገቡ እና የሕዝቡንም ዕድገት የሚፈልጉ ትልቅ ሰው ስለነበሩ በትምህርት ዙሪያ ያለውን ችግር ነገርኳቸው። "ሕዝቡ ወልዶ ተዋልዶ ሰባት ትውልድ ባየበት ምድሩ መንግስት አዲስ ባሰማራቸው መልክኞች ትምህርት ቤት እንዳይኖረው ተከለከለ።" አልኳቸው።

ቀኛዝማች ስዩም ሕዝቡን የሚወዱ የዘመኑንም አሠራርም የሚያውቁ ትልቅ ሰው ስለነበሩ ሕጋዊ ፈቃድ ያለው ትምህርት ቤት እንድንከፍት ምክር ሰጡኝ። በጊዜው እኔ የሕዝቡን ጨለማ ለመግፈፍ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ባምንም ቀኛዝማች ስዩም ጨምረው ትምህርት ቤት እንዲከፈት ተግተን እንድንሠራ እና ትምህርት የገበሬውን እና የባላባቱን ልጅ እኩል የሚያደርግ ሕዝቡን የሚያሳድግ ዋና መሣሪያ እንደሆነ መክረውኝ ወደ ሻሾን ተመለስኩ።

እንደተመለስኩም አዲስ በጨበጥኩት ተስፋ ተበረታትቼ ሳልውል ሳላድር የክፍለ ማኅበር መሪዎች ጋ ቀርቤ የቀኛዝማች ስዩምን ሃሳብ አካፈልኳቸው። እነርሱም በሃሳቡ ላይ በአንድ ድምፅ ተስማምተው እንዲሳኳ መጸለይ ጀመሩ። ለእኔም ጉዳዩን እንዳስፈጽም ውክልና ጽፈው ሰጡኝ።

እኔ በተሰጠኝ ውክልና መሰረት ደብዳቤ አዘጋጅቼ ለአውራጃው የትምህርት ሚኒስቴር ጽ/ቤት አስገባሁ። ጽሕፈት ቤቱም የአካባቢው ባላባት እና የአገር ሽማግሌዎች መስማማታቸውን ገልጸው የሚፈርሙበት ቅጽ ሰጥቶኝ ተመለስኩ። ይህንኑ ጉዳይ እንዴት እንደማስጨርስ እያሰብኩ እና እየጸለይኩ እያለም እግዚአብሔር ረድቶኝ የአገሩ ባላባት እና የአገር ሽማግሌዎች በአንድ ላይ ተሰብስበው አገኘኋቸው።

ነገሩንም ብልኃት በተሞላው አቀራረብ ገለጽኩላቸው። በመጀመሪያ "ከእኛ ከሻሾን ሰዎች መካከል ለምንድን ነው አንድ የተማረ ሰው ሆሳዕና ከተማ የማይኖረው? የዚህ አካባቢ ሰው ሆሳዕና ውስጥ ቤትም ዘመድም የለውም። ለምን?" ብዬ ጠየቅኋቸው። ሁሉም ዝም አሉ። "ከሌላ አካባቢ እና አገር ብዙ ሰዎች እየተነሱ በመላ ኢትዮጵያ ይኖራሉ። እኛ ግን እንኳን በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ልንገኝ በገዛ ከተማችን በሆሳዕና እንኳን አንድ ሰው የለንም" አልኳቸው።

"ስለሆነም እኔ ትምህርት ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ሄጄ ጥያቄ አቅርቤ የአገሩ ባላባት እና ሽማግሌዎች መስማማታቸውን ፈርመው ይላኩ ብለው ይህን ቅጽ ሰጥተውኛል" ብዬ አቀረብኩላቸው። እነርሱም ወዲያውኑ ያለ ምንም ተቃውሞ ተስማሙ። ከዚያም የኛ ቤተ ክርስቲያን ክፍለ ማኅበር በጠየቀው መሠረት አራት ትምህርት ቤቶች ሻሾን ውስጥ ባሉ አራት ቦታዎች በዶኢሻ፣ በኡርበጫ፣ በሻሞ እና በዋንችኮታ እንዲከፈቱ እኔ ባቀረብኩት ጥያቄ ተስማምቼ ባመጣሁት 18 ገጽ ቅጽ ላይ ሁሉም ፈርመው ማኅተም አድርገው ሰጡኝ። እኔም ያንን ይዤ መጣሁ። ከዚያም ቀኛዝማቹ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ሰነዱን አስገብተው ብዙ ቀን ራሳቸው ተመላልሰው በማስጨረስ ፈቃድ አውጥተው ስለ ሰጡኝ እኔም በደስታ ወደ ሻሾን ተመለስኩ።"

እዚህ ጋ ልክ የኛ ፈቃድ በወጣ ጊዜ ተጠይቆ ፈቃድ የተገኘበትን ሌላ ጉዳይ ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል። በዚያ ዓመት በሃዲያ ውስጥ እንዲሁ በብዙ ቦታ ትምህርት ቤቶች ለመክፈት ፈቃድ ስላልነበረ በአውራጃው ውስጥ ልዩ ልዩ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ልክ እኛ ለሻሾጎ እንደጠየቅነው አቶ አበበ ቡሼር የሚባሉ አንድ ታላቅ ሰው በከምባታና ሃዲያ አውራጃ 96 ትምህርት ቤቶች በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ስም እንዲከፈቱ ጥያቄ አቅርበው ማስፈቀድ ችለዋል።

አቶ አበበ ቡሼር በዚያ ዘመን የከምባታና ሃዲያ አውራጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በነገረ ፈጅነት እና በውክልና ያገለግሉ የነበሩ እነዚያ ትምህርት ቤቶችም እንዲከፈቱ በማድረግ ለዚያ ምድር ትልቅ ውለታ የዋሉ ታላቅ ሰው ናቸው።

ወደ እኛ ታሪክ ስንመለስም እኔ የድሉን ዜና ወስጄ እንደገና ለወከለኝ ክፍለ ማኅበር እንዳቀረብኩ በዚያ ዘመን የእንጨት ችግር ስላልነበረ ሕዝቡ ሁሉ ተባብሮ እንጨት ቆርጦ ከላይ በጠቀስኳቸው አራት ቦታዎች ትምህርት ቤቶች ተሠሩ። በዚህ ጊዜም ልክ በርናባስ ለጳውሎስ የአገልግሎት አጋር ሆኖ በየስፍራው አገልግሎቱን እንዲቀጥል እንዳስቻለው ለኔም በእሸንላ አጋሬ የነበረው አቶ አሾር አሁንም እንደተለመደው በጉልበቱ፣ በገንዘቡ እና በዕውቀቱ የተባበረ እውነተኛ አጋሬ ሆኖ ነበር።

እኛ ትምህርት ቤቶቹን ስንከፍት ፈቃዱን ለማግኘት ባስፈረምነው ቅጽ ላይ የፈረመው ባላባትም አንዱ ትምህርት ቤት እኛ ካቀድነው ውጪ በራሱ ደጃፍ እንዲከፈት ጥያቄ አቅርቦልኝ ነበር። እኔ ግን አሁንም በጥበብ ትምህርት ቤቶቹ የተከፈቱት በቤተ ክርስቲያን ጠያቂነት ስለሆነ ተጠያቂነቱም የቤተ ክርስቲያን ነው። አንተ ደጅም ቢከፈት አንተ ተጠያቂ ልትሆን አትችልም። ተባብረን ለመሥራትም አንተ ከእኛ ጋር ተሰብስበህ አታውቅም። ወይም ሁል ጊዜ በኛ ስብሰባ መገኘት አለብህ። እኛ ለትምህርት ቤቱ ተጠያቂ ስለሆንን እኛ የምንቆጣጠረው ቦታ መሆን አለበት ብዬ አሳመንኩት። በዚያ ላይም በዶኢሻ ያለው አንዱ ትምህርት ቤት ለእርሱ ቅርብ እንደሆነ አስረዳሁት። እርሱም መልካም አስቦ የጠየቀው ስላልነበረ ብዙም ሳይገፋበት ተወው።

ከዚያም ቤተ ክርስቲያን በደንብ መክራ ለትምህርት ቤቶቹ መምህራን መደበች። በአንዳንድ ቦታዎችም እኛው አስቀድመን ጀምረን በነበረው መልኩ ትምህርቱ ቀጠለ። እኔ በ1956 ዓ.ም ፈቃዱን ካወጣሁ በኋላም በ1957 ዓ.ም በአራቱም ቦታዎች ትምህርት ተጀመረ። የደርግ መንግስት ሥልጣን ይዞ እስከተወረሱ ድረስም እነዚያ ትምህርት ቤቶች በትምህርት መርኃ ግብራቸው (ካሪኩለማቸው) ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን አካትተው ሲያስተምሩ ቆይተዋል።

እኔም ሻሾጎ በነበረኝ ከሙሉ ጊዜ አገልግሎት የተለየ ቆይታ ይህንን ስኬት ስለሰጠኝ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። እነዚያ ትምህርት ቤቶች ዛሬ እስከ አስራ ሁለተኛ ድረስ ሁሉ የሚያስተምሩ እና በዚያ ምድር ላይ ትልቅ ተጽእኖ ያላቸው ሆነው ማየቱ

ታላቅ ደስታን ይሰጠኛል። በቅርቡም በኡርበጫ ያለው ትምህርት ቤት 50ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ሲያከብር የእኔን ውለታ በማስታወስ የክብር ተሸላሚ በማድረግ በስፍራው ባልገኝም የላኩልኝ የትልቅ ጋቢ ስጦታ ልቤንም አካሌንም ያሞቅልኛል።

---------------------//---------------------

*ኬዳሞ በሻሾን ምድር ወንጌልን እየሰበከና የአካባቢውን ሕዝብ በልዩ ልዩ ጉዳዮች እየረዳ ለሁለት ዓመታት ያህል ኖረ። በዚህ ጊዜ በተለይ ምድሩን እንደ ድቅድቅ ጨለማ የጀቦነውን እውቀት ማጣት እና ድህነት ለመከላከል ወንጌል መስበክ እና ትምህርት ማስተማር ዋነኛ መሣሪያ እንደሆነ ያምን ነበር። በዚህም መሠረት እግዚአብሔር በዘመዶቹ መካከልም ሆነ ለምድሩ ብርሃን አድርጎት ሰዎች በወንጌል እያመኑ ወጣቶች እና ታዳጊዎች ከመሃይምነት ይላቀቁ ጀመር። ከዚህም የተነሳ ለብዙዎች የተሰፋ ብርሃን ፈነጠቀላቸው። ብዙዎችም የራሳቸውን እና የትውልዳቸውን ሕይወት አቅጣጫ የሚቀይር መንገድ ጀመሩ።*

*ሻሾን ዛሬም ድረስ በብዙ ቦታዎች እንደ መብራት፣ መንገድ እና ንጹህ ውሃ የመሳሰሉ የዘመናዊነት መገለጫ የሆኑ መሠረተ ልማቶች ያልተስፋፉባት ምድር ናት። ይሁንና በዚያ ዘመን በወንጌላዊ ኬዳሞና መሰል አስተዋይ ሰዎች የተጀመሩ ትምሕርት ቤቶች ካደረጉት እገዛ የተነሳ የሻሾን ወረዳ ዛሬ በመላ ሃዲያ ከሚገኙ ወረዳዎች በትምህርት ቤት ብዛት ሁለተኛ ደረጃ የያዘች መሆኗን ሲ.ኤች.ኤስ.ኤፍ.ኤስ የተሰኘ ተቋም በዞኑ አጠቃላይ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ላይ ያደረገው ጥናት አረጋግጧል።*

# ምዕራፍ ፲፰

# ወደ ቀደመው ጥሪ መመለስ

በዚህ መልኩ እኔም ለአካባቢዬ ማኅበረሰብ ጠቃሚ ሰው ሆኜ ምንም እንኳን አስቀድሜ የወንጌሉን አደራ ተሸክሜ በአገሩ ሁሉ እንድዞር ራሴን ለጌታ አሳልፌ ሰጥቼ የነበረ ቢሆንም በምሠራው ሁሉ ተደስቼ ኑሮዬን ቀጠልኩ። በግብርናው በኩል ስኬታማ ሆነን ኑሮአችንም የተመቸ ሆኖልናል። በዚሁ ጊዜም በ1957 ዓ.ም ክረምት ላይ በምሠራው ሥራ ላይ በተጨማሪነት 100 ፍየሎች ገዝቼ ላረባ እና በጥቂት ዓመታት ውስጥ በብዙ እጥፍ ቁጥራቸውን አሳድጌ ብዙ ትርፍ ላገኝ አቀድኩ።

በዚህ ሁሉ ምቹ የሚመስል ሁኔታ ውስጥ ሳለሁ ግን አስቀድሞ የጠራኝ ጌታ ሊተወኝ አልወደደም እና በዚያ ኃይለኛ ክረምት በወርኃ ሐምሌ አቶ በቀለ ወርቁ የሚባል ወዳጃችን የሆነ ወንጌላዊ ከከምባታ የስምንት ሰዓት መንገድ በእግር ተጉዞ ወደ እኛ ቤት መጣ። ይህ እኔ እየተጓዝኩበት የነበርኩበት ከቃል ኪዳን የወጣ አቅጣጫ እንዲመልሰኝ ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው በዚያ የከምባታ ሰው ወደ ሻሸጎ በማይወርድበት ወባ እና እንደ ተስቦ ያለ ሌላም በሽታ የበዛበት የክረምት ጊዜ ትልቅ ዋጋ ከፍሎ የሞሉ ወንዞችን አቋርጦ ቤቴ ድረስ መጣ። እኔ ለሥራ ወጥቼ በነበረበት ጊዜ ቤት ደርሶ ከባለቤቴ ጋር ሲጫወት እና ሲመክራት አሳለፈ። ምሽቱንም እኔ መጥቼ እራት ከበላን በኋላ "እግዚአብሔር አንተን ይፈልግሃል" አለኝ። እስከ ሌሊቱ ሰባት ሰዓት ድረስም ስንማከር እና ስንሟገት አመሸን። እኔም አቶ ወርቁ ከእግዚአብሔር እንደተላከ ተረድቼ "ታዲያ ምን ላድርግ?" አልኩት። እርሱም ዱራሜ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቼ ያቆምኩትን ትምህርት መቀጠል እንዳለብኝ ስለመከረኝ በዚሁ ሃሳብ ተስማምተን እዚያው ተንበርክከን ጸልየን ተለያየን።

አቶ ወርቁ በማግስቱ ተመልሶ ወደ ዱራሜ ሄደ። መማር ካቋረጥኩ ከሰባት ዓመታት በኋላም ትምህርቴን እንድቀጥል የሚጠይቅ ደብዳቤ ራሱ ከሚ/ር ካይዘር አስጽፎ ጥያቄው ወደ ክፍለ ማኅበራችን መጣ። እኔም እንደገና ትቼው ወደነበረው የአገልግሎት አቅጣጫዬ እና ወደ ቀድሞ ጥሪዬ ተመለስኩ። እግዚአብሔርም በሄድኩበት ሳይተወኝ ሊመልሰኝ አቶ ወርቁን የመሰለ መልካም ሰው ብዙ ዋጋ ከፍሎ እንዲያገኘኝ አደረገ።

እኔም ወደ ልቦናዬ ተመልሼ በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመግባት እንዴት በእንፋቅቅ ሄጄ መሪዎችን እንደለመንኩ ከዚያም በቢቾ በትጋት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በመማር እና ለአገልግሎት በመዘጋጀት ላይ እያለሁ ቤተ ዘመድ ተሰብስቦ "ክብት ጠፋ፤ ንብረት ወደመ" ሲለኝ "እኔን እንደሞትኩ ቁጠሩኝ" ብዬ የጨከንኩት ሁሉ ትዝ አለኝ። ወንጌልን ተሸክሜ ዓለምን ለመዞር ቃል የገባሁት ሰው በምቾት ተከብቤ በአካባቢዬ ተወስኜ መቅረት እንደሌለብኝም አመንኩ። እንደገናም ቃል ኪዳኔን ለማደስ እና ጌታ ወደ ጠራኝ ሁሉ እየሄድኩ በችግር እና በመከራ ሳይቀር ለማገልገል ወሰንኩ። ጌታም ወዲያው ወደ ቀደመው የአገልግሎት ሕይወት የምመለስበትን መንገድ አዘጋጀ።

# እንደገና ትምህርት

አቶ ወርቁ እኔን ከተሳሳተ አቅጣጫ እንድመለስ መክሮ ከተመለስ ቀናት ተቆጠሩ። ወደ እኔ ለመምጣት ዋጋ እንደከፈለው ሁሉ ቶሎ ወደ ትምህርቴ እንድመለስም ሳይውል ሳያድር ጥያቄውን አቅርቦ ወዲያውኑ በ1958 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ ዱራሜ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቴን እንድቀጥል የሚጠይቅ ደብዳቤ ከዱራሜ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መጣ። የኔ ክፍለ ማኅበርም ከዚህ ቀደምም ራሳቸው ልከው ትምህርቱን ያስጀመሩኝ ስለሆኑ እንድማር ፈቀዱ። እኔ ግን ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ አሁንም አንድ ጥያቄ አቀረብኩ።

ከዚህ ቀደም እኔ ጠይቄ እነርሱ በፈቀዱልኝ መሰረት የሁለቱን ዓመት የትምህርት መርኃ ግብር በአንድ ዓመት ጨርሼ ነበር። አሁንም እንዲሁ እንደገና ወደ ትምህርት የምመለሰው የሁለቱን ዓመት ትምህርት በአንድ ዓመት እንድማር ከፈቀዱ ብቻ እንደሆነ ነገርኳቸው። ባይሆን ትምህርቱን ጀምሬ የሚከብደኝ ከሆነ ክርሶቹ እንዲቀነሱ ተስማምተን ወደ ትምህርት ቤት አመራሁ።

ዱራሜ ትምህርቱን ስጀምርም እችላለሁ ብዬ እንደጠየቅሁት ብዙ ዓመታት ከትምህርት ተለይቼ መቆየቴ ሳይጎዳኝ በሁሉም ጥሩ ውጤት እያመጣሁ መማር ቻልኩ። ከመቶ 95 እና 85 ወረድ ሲልም 75 እያገኘሁ መዝለቤን ቀጠልኩ። ትምህርቱም ለወደፊቱ አገልግሎቴ የጠቀመኝ፣ በጣም የሚያጓጓ እና አስደሳች ነበር።

ትምህርት ቤቱን የሚያስተዳድሩት እነ ሚስተር ካይዘርም በጣም ጎበዝ መምህራን ነበሩ። ዱራሜ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበረን ቆይታ ባለቤቱን እና ልጆቼን ይዤ ስለሄድኩ ትምህርት ቤቱ በሰጠን ቤት እየኖርን ነበር የምማረው። ከዚህም ባሻገር እኔ በሻሸን ቆይታዬ ባፈራሁት ገንዘብ የገዛኋቸው በቅሎዎች ስለነበሩኝ ወደ ዱራሜም የሄድኩት በቅሎዬን ይዤ ነበር። ለኑሮ የሚያስፈልገንንም ቤተ ክርስቲያን እንደ አገልጋይ ቆጥራ በወር ከምትከፍለን 10 ብር ድጎማ በተጨማሪ እኔ በራሴ በቅሎ እየተመላለስኩ በሌላ በቅሎ እየጫንኩ እህል እና ቅቤ ከሻሸን አመጣ ነበር።

ትምህርቱን በጥሩ ሁኔታ እየተማርኩ በትምህርት ቤቱ ግቢም እንደ አንድ ትልቅ አገልጋይ ተቆጥሬ ተከብሬ ነበር የምኖረው። በአብዛኛው ሰንበትም በዙሪያው ባሉ ቤተ ክርስቲያናት ለአገልግሎት እየተጠራሁ አገለግል ነበር።

ዓመቱም በፍጥነት በመገባደዱ የዱራሜ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተጠናቅቆ ለምረቃ መዘጋጀት ጀመርን። እኔም እንደገና ወደ ታላቅ ጥሪው የመለሰኝ እግዚአብሔር ለእኔ ምን ዓይነት ቀጣይ የአገልግሎት ዘመን እንዳዘጋጀልኝ ስላላወቅሁ ወደፊት መሥራት ያለብኝ ምን እንደሆነ ማሰብ እና እግዚአብሔርም በምን መልኩ እንዳገለግለው እንደሚፈልግ ለማወቅ ቀድሞ እንዳደረግሁት ሁሉ በትጋት መጸለይ ጀመርኩ።

# ምዕራፍ ፲፮

# ወደ ቦቢቾ መሻገር

ጊዜው ኬዳሞ እንደገና ወደ ዱራሜ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሳይገባ በፊት ከነበሩት ዓመታት አንዱ ነው። እትብቱ በተቀበረባት ሻሾጎ እና በዙሪያዋ እያገለገለ ያለበት ወቅት ነበር። በአንድ ወቅት በመጀመሪያ ፊደል ሊያስቆጥር ካሰባሰባቸው 170 ተማሪዎች መካከል አንዱ የነበረው እና ኋላም ፈለጉን ተከትሎ የወንጌል አገልግሎት አጋሩ ከሆነው አቡዬ ጋር ወደ ሆሳዕና እና ቦቢቾ ማዕከል ሄዷል። በጊዜው ወንጌልን ለመስበክ እዚህም እዚያም ተፍ ተፍ የሚለው ኬዳሞ ለወንጌል ስብከት ሲቆም የሚለብሰው ሙሉ ልብስ እንደሚያስፈልገው አምኖ ያለችውን 6 ብር ይዞ ከቤት ወጥቷል። ሁለቱ የወንጌል አገልግሎት ያጎዳኛቸው የአንድ ቀዬ ተወላጆች የሐዲያ ህዝብ ዋና ከተማ በሆነችው ሆሳዕና ከተማ አብረው ሲዘዋወሩ ቆይተው ኬዳሞ እንደሚያስፈልገው ያሰበውን ሙሉ ልብስ ለማሰፋት ብትን ጨርቅ ገዙ።

ይሁንና ኬዳሞ በያዘው 6 ብር የገዛውን ብትን ጨርቅ ሙሉ ልብሱ ተሰፍቶ ሲያልቅ 6 ብር ከፍሎ ሊወስድ ተስማምቶ ጨርቁን ለልብስ ሰፊ አስረከበ። ይህንን እና ሌሎች የየግል ጉዳዮቻቸውን ከፈጸሙ በኋላም ኬዳሞ እና አቡዬ ተያይዘው በዚያ ዘመን ለምንም ጉዳይ ቢሆን ወደ ሆሳዕና የመጣ አገሊጋይ ቀርቶ አዲስ አማኝ ሳይረግጠው ወደማይመለሰው የኬዳሞ የቀድሞ ትምህርት ቤት መገኛ ቦቢቾ ማእከል አመሩ።

ቦቢቾ ቅጥር ግቢ ከደረሱ በኋላም በማዕከሉ በሚስዮናዊነት በማገልገል ላይ የነበሩት ሚስ ማክለክ ተቀብለው አስተናገዷቸው። በወቅቱ ሚስ ማክለክ ቦቢቾ ግቢ ውስጥ ባለ በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች በውጪ ዜጎች የቤት አሠራር ስልት በተሠራ ቤት ይኖሩ ነበር። ሻሾጎ በመስኮት አልባ የሣር ጎጆ ቤቶች ውስጥ የቤት እንስሶቻቸውን ሙቀት እየተጋሩ መኖር የለመዱት ኬዳሞ እና አቡዬም ይሄንን በሚስዮናውያኑ የተሠራ የቆርቆሮ ጣራ የለበሰ ዘመናዊ ቤት እያደነቁ ይስተናገዱ ገቡ።

በተለይም በዚያ ወቅት ከሻሾጎ እምብዛም ርቆ ሄዶ የማያውቀው አቡዬ መደነቅ ደግሞ እጅግ የበዛ ነበር። ኬዳሞ ግን ከቤቱም ሆነ ከሚስ ማክለክ መስተንግዶ ይልቅ ውስጡን በአድናቆት እና በምስጋና የሞላው አንድ ነገር ነበር። ሚስ ማክለክ ከኬዳሞ ምንም ጥያቄ ባይቀርብላቸውም ልክ እግዚአብሔር የኬዳሞን ልብ አንብቦ በጆሮአቸው ሹክ ያላቸው ይመስል ኬዳሞ ሆሳዕና ድረስ መጥቶ ለልብስ መስፊያ የጎደለውን እና

በእምነት ሲያገኝ የሚጠባበቀውን 6 ብር ከመኝታ ቤታቸው አምጥተው ሰጡት። ኬዳሞ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸውን ሚስዮናዊት ባርኮ ለታመኑት ድንቅ አድራጊ የሆነው አምላኩን እያመሰገነ በታላቅ መደነቅ ተሞልቶ ነበር።

ሁለቱ የሻሸን ሰዎች ቆይታ እንዲህ መደነቅ የሞላበት ሆኖላቸውና በሚገባ ተስተናግደው በደስታ ከሚስ ማክሌክ ቤት ወጡ። በዚሁ ጊዜ የገቡበት ቤት ዘመናዊነት እጅግ ያስደነቀው አቡዬ ገና የቤቱን ደጃፍ እንደተሻገሩ በማድነቅ ይናገር ጀመር። "አቤት እንዴት የሚገርም ቤት ውስጥ ተቀምጠን ቆየን! ውስጡ ውጪ ያለን ያህል ብርሃን አለው። በዚያ ላይ መስኮቱ ብርሃኑን እንጂ ንፋሱን አያስገባ (የቤቱ መስኮት ባለ መስታወት ስለነበር)፤ የሚጠጣው ውሃ በዕቃ ሳይሆን እንደ ምንጭ ውሃ እዚያው የሚፈስስበት፤ መጸዳጃ ቤት ሲያስፈልግ እዚያው ቤት ውስጥ የሚጸዳዱበት፤ ግን ሽታ የሌለው ... ምን ዓይነት ተዓምረኛ ቤት ነው!' እያለ ቤቱን አደነቀ። "የኛ የሻሸን ቤት በጭስ ታፍኖና ጠቁሮ የሚታየው ሁሉ ጥቀርሻ ነው። ይህ ቤት ግን ውስጡም ውጪውም ነጭ ነው።" እያለም አከለ። ወዲያውም ወደ ኬዳሞ ዞሮ "ኬዳሞ መቼም በእንደዚህ ዓይነት ቤት የኔና ያንተ የልጅ ልጆች ይኖሩ ይሆናል።" ሲል ተናገረ። በዚህ ጊዜ በዚህ ዕለት ጭምር የፈለገውን እያደረገለት ያስደነቀውን እግዚአብሔር የተማመነው ኬዳሞ "ለምን የልጅ ልጆቼ? እኔ ራሴ አንድ ቀን በእንደዚህ ዓይነት ቤት እኖራለሁ!' አለ።

ኬዳሞ እና አቡዬ ይህን በተባባሉ በጥቂት ዓመታት ውስጥም ኬዳሞ ዱራሜ ገብቶ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቱን ተከታትሎ በማጠናቀቁ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከተመረቀ በኋላ ምን መሥራት እንዳለበት ይጸልይ እና ያስብ ጀመር። ከዚህ ቀደም ለወዳጁ አቡዬ "አንድ ቀን በእንደዚህ ዓይነት ቤት ውስጥ እኖራለሁ።" ያለውን ሃሳብ መፈጸሚያ ቀን እንደሚደርስ ስላልገመተም ሁል ጊዜ ልቡ ወደ ሚመላለስባት ሻሸን ተመልሶ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የመክፈት ሃሳብ ያወጣና ያወርድ ጀመር። ልክ ድሮ በእረኝነቱ ስፍራ በእግዚአብሔር ፊት እንደጸለየው አሁንም በትጋት ይጸልይ ገባ። በዱራሜ ጠዛ ግቢ ባለች ወደ አንዲት የጸሎት ክፍልም በተደጋጋሚ እየገባ በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ የወደፊት የአገልግሎት አቅጣጫውን ይጠይቅ ነበር። "ጌታ ሆይ እኔ ወደ ሻሸን ተመልሼ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መክፈት አስባለሁ። ያንተስ ፈቃድ ምንድን ነው?' እያለ በተደጋጋሚ በዚያች ክፍል ውስጥ የጸለየውን ጸሎት እና የጸሎት ክፍሏን ዛሬም ድረስ እያስታወሰ ዱራሜ በሄደ ጊዜ ይጎበኛታል።

አንድ ቀን ኬዳሞ በዚያችው የጸሎት ክፍል ውስጥ እየጸለየ እያለ እግዚአብሔር መልሱን ላከና የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አባት የሆኑት አባጎሌ፣ የበጎ ሚስዮን ማዕከል አስተዳዳሪ የሆኑት ሚስዮናዊ ሚስተር ዳይ እና አቶ ሞሉሮ ኬዳሞን ለማናገር ዱራሜ ድረስ መጡ።

---------------------//---------------------

እግዚአብሔር ጸጋውን አብዝቶልኝ ዱራሜ "ተማሪ" የሚለውን ስም ይዤ ነገር ግን በዱራሜ እና በከምባታ ምድር እንደተማሪ ሳይሆን እንደ አንድ አገልጋይ አክብሮት እየሰጡኝ በኑሮ ሁኔታም የሚያስፈልገውን ሁሉ እያሟላን ከቤተሰቤ ጋር ዓመቱን አሳለፍን። ትምህርቱም በመልካም ሁኔታ ተጠናቀቀ። በዚሁ ጊዜም አስደናቂ የአገልግሎት በሮችን በልዩ ልዩ ስፍራዎች የከፈተልኝ ጌታ አሁንም በኔ ፈቃድ ሳይሆን እርሱ ወደ ወደደው እንደመራኝ በብርቱ መጸለይ ጀመርኩ። እግዚአብሔርም በተደጋጋሚ ሲመራኝ እንደነበር እንዲሁ ፈቃዱን ገለጸልኝ።

አንድ ቀን በዚሁ የወደፊት የአገልግሎት አቅጣጫዬ ዙሪያ ስጸልይ በሻሸን ክፍለ ማኅበር ምንም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስላልነበረ በሻሾን መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለማቋቋም የነበረኝን ሃሳብ ይዤ በእግዚአብሔር ፊት ቀረብኩ።

እግዚአብሔር ግን እኔን ለበለጠ እና ለሰፊ ሥራ ይፈልገኝ ነበር። በዚያን ዕለት ጸሎቴን ሳልጨርስ አባ ጎሴ፣ ሚ/ር ዳይ እና አቶ ሞሎሮ እኔን ፈልገው መጥተው ጠዛ ማዕከል ገቡ። ወዲያውኑም ሚ/ር ዳይ እማክኝነት ወደ ቦቢቾ መጥተህ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምክትል ዳይሬክተርነት እና በአስተማሪነት እንድታገለግል ፈልገንሃል ብለው ነገሩኝ። ከማገለግላት የሻሾን ክፍለ ማኅበር ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጋር ተማክሬ ምላሽ እሰጣለሁ አልኩ።

ከዚያም በነገሩ ላይ መጸለይ ጀመርኩ። ወዲያውኑም ሃሳቡን ለሻሾን ክፍለ ማኅበር መሪዎች ነገርኩ። የነገርኳቸውም በቢቾ እንድሄድ የመፈለጌን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን እኔ ስመለስ ሻሾን ላደርግ ያሰብኩትን ዕቅዴን ጭምር ነበር።

የሻሾን ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም በጉዳዩ ላይ ካሰቡበት በኋላ "እኛ (ሻሾንዎች) ቦቢቾ ድረስ መጥተን መጽሐፍ ቅዱስን እንማራለን። አንተ እዚያ ብትገባ ይሻላል" ብለው እኔ ብገባ እንደሚሻል ወሰኑ። መሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስ መማር ያለባቸውንም ቦቢቾ ልከን እናስተምራለን በማለታቸው በ1959 ዓ.ም ጓዜን ጠቅልዬ ቤተሰቤን በሙሉ ይዤ ወደ ቦቢቾ ማዕከል አቀናሁ። መለስ ቀለስ እያልኩ ሳገለግላት የኖርኩትን የትውልድ ቀዬዬን ሻሾንንም ከዚያ በኋላ በቋሚነት ላልኖርባት ተሰናበትኳት። ሁል ጊዜ ስሟን እና ትዝታዋን በህሊናዬ እኑሬ እግዚአብሔር በቀየሰልኝ አቅጣጫ መንገዝ ቀጠልኩ። ቦቢቾ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምክትል ዳይሬክተር እና መምህር ሆኜ ማገልገልም ጀመርኩ።

## የተገራው የሻሾን ወይፈን ሁለገብ አገልግሎት በቦቢቾ

እግዚአብሔር ለወንጌል አገልግሎት ከጠራኝና እኔም ታዝዤ ማገልገል ከጀመርኩ ሁለት አስርት ዓመታት ለመድፈንም ጥቂት ብቻ ቀርቶኛል። በዚሁ ጊዜም ጌታ ፈቅዶ በብዙ ቦታ ማገልገል መቻሌ ለኔ በጣም አስደሳች እና አስደናቂ ነበር። ዲላ፣ ማረቆ፣ ኩየራ፣ ዱራሜ እየዞርኩ በተለያዩ አጋጣሚዎች ማገልገል ችያለሁ። በእነዚህ ሁሉ

ጊዜያት ውስጥም በእነዚህ አካባቢዎች ለተወሰነ ጊዜ እቆያለሁ እንጂ በመጨረሻ ተመልሼ የትውልድ መንደሬ ሻሾጎ መግባቴ አይቀርም። በእነዚህ ሥፍራዎች በምቆይበት ጊዜ ሁሉ በአብዛኛው የሚያስፈልገኝ ነገር እናቴ ካሉበት የሻሾጎው ያልተዘጋ ቤቴ ይላክልኛል። እኔም አጋጣሚ ቡተገኘ ቁጥር ለእረፍትም ሆነ ለጉዳይ ወደ ሻሾጎ መመለስ በደስታ የማደርገው ነገር ነበር። አሁን ግን ቁርጬ ከሻሾጎ የምለይበትና አንድ ምዕራፍ የምርቅበት ዘመን መጣ። ከሻሾጎ የአንድ ቀን የእግር መንገድ (35 ኪሎ ሜትር ያህል) የምትርቀው ቦቢቾ ቋሚ ቤቴ እንድትሆን እግዚአብሔር በመወሰኑ እኔም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ወደ ቦቢቾ ለመዝመት ተነሳሁ።

የዱራሜ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተጠናቅቆ ከተመረቅን በኋላ በ1958 ዓ.ም መጨረሻ ወደ ሻሾጎ ተመልሰን ክረምቱን አሳለፍን። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ትምህርቴን ካጠናቀቅኩ በኋላ ሳስበው የኖርኩት በሻሾጎ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የመክፈት እቅዴ ቀርቶ በቦቢቾ አዲስ ለሚጠብቀኝ የአገልግሎት ኃላፊነት እራሴን እና ቤተሰቤን አዘጋጀሁ። ከዚያም እናቴን እና ባለቤቴን ሳስታምም ጀምሮ እናቴ ጋ እያደገች ያለችውን የእናቴ የበስተርጅና ልጅ የሆነችውን የመጀመሪያ ልጄን ድንቅነሽን ተሰናበትን። ይህቺ ልጄ ከእናቴ ጋር ገጠር መቅረቷ ያሳሰባት ባለቤቴ ታደለች በተደጋጋሚ ወደ ከተማ መጥታ ከኛ ጋር እንድትኖር ብትለምናትም ልጄ ግን ከአያቷ አልለይም ብላ እናቴ እስከሞቱበት ዕለት ድረስ አብራ ሻሾጎ ኖረች። አሁንም እዛው ሻሾጎ የራሷን ኑሮ ትኖራለች። ታደለች እና እኔም አምስት ልጆቻችንን ይዘን ጓዛችንን እና ራሳችንን በበቅሎ እና በፈረስ ጭነን ወደ ቦቢቾ አመራን። እትብቴ የተቀበረባት ሻሾጎንም ከዚህ በኋላ ለአጭር ጊዜ ቆይታ ለዘመድ ጥየቃ እና ለአገልግሎት ካልሆነ በስተቀር በቋሚነት ለመኖር ሳልመለስባት ተሰናብቻት ሄድኩ።

ቦቢቾ የሚስዮን ማዕከል ውስጥ የምንኖርበት ቤት ተሰጥቶን በዚያው ቅጥር ግቢ ውስጥ እየኖርን አገልግሎቴን ጀመርኩ። በጊዜው ገና ዱራሜ እያለን ሚ/ር ዳይ እና እነ አባ ጎሌ መጥተው በነገሩኝ መሠረት እኔ ከሚ/ር ዳይ ቀጥዬ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ ምክትል ዳይሬክተር ነበርሁ። ከዚህ በተጨማሪም የግቢው ኃላፊ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ የተለያዩ ኮርሶች አስተማሪ፣ በቤተ ክርስቲያን ስም የተገዛ መሬት ስለነበርም የመሬቱ አስተዳዳሪ፣ የክፍለ ማኅበር ቤቶች እንግዳ ቤትና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳደር አማካሪ በመሆን ብዙ ተደራራቢ ሥራዎችን እሠራ ነበር።

በአጠቃላይ የግቢው ኃላፊ ስለሆንኩም ከጥበቃ እስከ ሌሎች ሠራተኞች ድረስ ያሉትን ሁሉ ለመቆጣጠር ከሥራ ሰዓት ውጪ ሳይቀር እስከ ምሽቱ 7 ሰዓት ድረስ እያመሸሁ ለመስራት እገደድ ነበር። ይህን ሁሉ ሥራ ስምሠራበትም በዚያ ዘመን ጥሩ ሊባል የሚችል በወር 65 ብር ደመወዝ ይከፈለኝ ነበር። ሆኖም በጊዜው የኛ ቤት የአውራጃው ማዕከል በሚገኝበት ቅጥር ግቢ ውስጥ በመሆኑ ለቤተ ክርስቲያን ጉዳይ፣ ለሕክምና ወይም ለራሳቸው ጉዳይ የሚመጡ እንግዶች እኛ ቤት ስለሚያርፉ ገንዘቡ

ፈጽሞ ሊበቃን አልቻለም ነበር። እኛ ሙሉ በሙሉ ከገጠር ስለተለየን አንዳንድ ጊዜ እናቴ ከሚልኩልን በርበሬ እና ጥቃቅን ነገር በስተቀር ሌላ ነገር አልነበረንም።

በዚሁ ጊዜ እኔ በዙሪያ ገባችን ባሉ ቤተ ክርስቲያናት በትላልቅ የማኅበር ስብሰባዎች በከምባታ እና ከዚያ ተሻግሮ ባሉ አውራጃዎች ሁሉ ሳይቀር እየተጋበዝኩ እየሄድኩ ወንጌል አስተምር ነበር።

በ1959 ዓ.ም አስተዋይ የሆኑትና በሃዲያ ምድር 96 ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ ምክንያት የሆኑት አቶ አበበ ቡሺሮ ጥያቄ አቅርበው ከቦቢቾ ሆሳዕና እየተመላለስኩ በአንድ ሆቴል ክፍል ውስጥ ሰባት ያህል ሰዎችን የማታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አስተምር ጀመር። በዚያ ጆብ በሞላበት የቦቢቾ መንገድ ማታ ማታ የሚያጅቡኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ተማሪ ልጆችን ባትሪ ይዤ እየሄድኩ አስተምር እና ምሽቱን እመለስ ነበር። ይህ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ምሽት የማስተምረው ትምህርት በቋሚነት ቀጥሎ እኔ ሆሳዕናን እስከለቀቅኩበት 1965 ዓ.ም ድረስ በመካሄድ ላይ ነበር። ትምህርቱ በሰባት ሰዎች ተጀምሮ ተማሪዎቹ 15 ስለደረሱ የሆቴሉ ክፍል ጠበበን እና ወደ ራስ አበበ ትምህርት ቤት ቋዛውሮ ማስተማር ቀጠልኩ። ይህንን ትምህርት ሳስተምር ቆይቼ ወደ አዲስ አበባ ተዛውሬ በ1965 ዓ.ም ሳቆም ይማሩ የነበሩት ተማሪዎች 36 ነበሩ።

በቦቢቾ ማዕከል የነበረን ቆይታ እየጨመረ በሄደ ቁጥርም እኔ በተለያዩ ስፍራዎች የማገለግለው አገልግሎት እየሰፋና ከቦታ ቦታ መዘዋወሬም እየጨመረ ይሄድ ነበር። ወላይታ፣ ጌዴኦ (ዲላ)፣ ሲዳማ ዋት፣ ወሊሶ በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ እየሄድኩ ኮንፍራንስ ላይ የማገለግልባቸው ቦታዎች ነበሩ። ወደ መጨረሻዎቹ ዓመታት ደግሞ አዲስ አበባ ሁሉ በልዩ ልዩ ቦታዎች እየተጋበዝኩ አስተምር ጀመር።

በአገልግሎቴም ሆነ በሥራ ኃላፊነቴ እግዚአብሔር እየረዳኝ ብዙ ፍሬ እያፈራሁ ነበር። በኃላፊነቴ በብዙ ሰዎች ፊት እግዚአብሔር ሞገስ ሰጥቶኝ ነበር። ለዚህም ዋናው ቁልፍ እኔ ሥራዬን በትጋት እየሠራሁ ሁል ጊዜም እግዚአብሔር አጥብቄ እንዲረዳኝ እጸልይ ነበር። ከባለቤቴ ከታደለች ጋር ለብቻ እና ከልጆቻችን ሁሉ ጋር በጋራ የእግዚአብሔርን ቃል እናጠና እና እንጸልይም ነበር። ግቢ ውስጥ አብረን በምንሠራ ሠራተኞች መካከልም ጥሩ ኅብረት ነበረን። ቦቢቾ ግቢ ያለን አገልጋዮች ዓርብ ማታ ተሰብስበን የምንጸልይበት የጸሎት ጊዜ ነበረን። ይህንን ለብዙ ጊዜያት የቆየ ጸሎት በርትተን እየጸለይን እያለም አንድ ዕለት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ባለንበት ቦቢቾ አካባቢ እና በዙሪያው ባሉ መንደሮች ወንጌል እንዳልተሰበከ ተናገረን። በጊዜው ይህንን ጉዳይ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አካፈልኳቸውና ዘወትር ሐሙስ የወንጌል ሥርጭት ዘመቻ ልናደርግ ተስማማን።

በዚህ ተልዕኮ ተካፋይ ሊሆኑ ፈቃደኛ የሆኑትን በሙሉ በ3 ቡድን ከፍዬ እንዲደራጁ አደረግሁ። እያንዳንዱ ቡድንም ወንጌል የመስበክ፣ ፊደል የማስቆጠር እና ያመኑትን መጽሐፍ ቅዱስ የማስተማር ሥራ እንዲሠሩ ከመደብኩ በኋላ ተነሰተን በአካባቢው

እየዞርን በትጋት እናገለግል ነበር። እግዚአብሔር ረድቶንም በአጭር ጊዜ ውስጥ በ5 ቦታዎች የጸሎት ማቢያዎች ተተክለው አገልግሎት መስጠት ጀመሩ።

ከዚሁ ጎን ለጎን ሆሳዕና ከተማ የሚካሄድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትም በመልካም ሁኔታ መካሄዱን ቀጥሎ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ይማሩ ነበር። በዚያ ጊዜ ከማስተምራቸው ተማሪዎች መካከልም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሳይቀሩ በድብቅ መጥተው ይማሩ ነበር። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚያገለግሉ ፊንሐስ እና ወልደ ጊዮርጊስ የሚባሉ ወንጌልን የተጠሙ ሁለት ወንድሞች ከእነዚሁ መካከል ነበሩ። ከዚያም በምሽቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የዘሌዋውያንን መጽሐፍ እያስተማርኩ በነበረበት ወቅት እነዚሁ ተማሪዎች "በኢትዮጵያ ውስጥ ይህንን መጽሐፍ በሚገባ እንዲህ ሊያስተምር የሚችል የለም። ስለዚህ እኛ ካህናቱንና ቄሶቹን እንሰበስብና አንተ አስተምር አሉኝ።"

በዚህ ጊዜ ነገሩ ጥያቄ ስለፈጠረብኝ በሰፊው ሕዝብ በተሰበሰበበት በተለይም የኦርቶዶክስ አገልጋዮችን ማስተማር እስጊ ስለነበር ጉዳዩን ለከምባታ እና ሃዲያ አውራጃ መሪዎች አሳወቅሁ። እነርሱም "ተው ትታሠራለህ" ብለው ቢመክሩኝም እኔ ግን የሰዎቹን ጥማት እና ጉጉት አይቼ "እሥራት ምን ያስፈራል? ስለወንጌል መታሰር ያለ ነው።" ብዬ ለማስተማር ወሰንኩ።

በራስ አባተ ኅሎ ትምህርት ቤት አዳራሽ ውስጥ ከ200 በላይ ሰዎች ተሰብስበው የአውራጃው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ጳጳስ ስህተት ካለ ሊይዙኝ በተቀመጡበት የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ፣ የፖስታ ቤት ሹም፣ የማዘጋጃ ቤቱ ጸሐፊ፣ የከተማ የሕዝብ ኃላፊ እና የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሥነ ጽሑፍ ኃላፊ በታዛቢነት እና ችግር ካለም ለምስክርነት በተገኙበት እሁድ እሁድ ከሰዓት በኋላ ከሰባት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት በስፋት አስተማርኩ። ይህ ትምህርት እኔ ቦቢቾ በምኖርባቸው ጊዜያት ሁሉ እየተካሄደ ለ4 ዓመታት ያህል የቆየና አስደናቂ ፍሬ የነበረው ነው። ብዙ ሰዎች በእሁድ ከሰዓቱ የትምህርት ሰዓት መጽሐፍ ቅዱስ ይማሩ እና ማክሰኞ እና ሐሙስ በሚካሄደው የማታ ትምህርት ጊዜ መጥተው ጌታን ይቀበሉ ነበር።

ፊንሐስ እና ወልደ ጊዮርጊስ ፍጹም ተለውጠው ስለነበርም ሁል ጊዜ ቦቢቾ እየመጡ አብረን እንጸልይ ነበር። አንድ ጊዜ ወልደ ጊዮርጊስ "እናንተ እንደ ኤሊ ሽክም የነበረውን ቋጥኙን ድንጋይ ሰብራችሁ ወጥታችኋል፤ እኛ ግን ይኸው በድንጋዩ ውስጥ ነን ምን ይሻለናል?" ብሎ እያለቀሰ መጸለያችንን አስታውሳለሁ።

እነዚህ ሁለት በወንጌል ያመኑ ወንድሞች እውነትን ለመግለጥ ይጥሩ ስለነበር አንድ ዕለት ፊንሐስ በአውራጃው ቤተ ክህነት ስብሰባ ላይ በሮሜ 1፡17-32 ላይ ያለውን ሃሳብ መሠረት አድርጎ "ሌላ ነገር ማምለክ አይገባም" ብሎ ሰበከ። በዚህም የከተማው ቄሶች በሙሉ ተቃውመው ስለተነሱበት እኛም እርሱን በመደገፋችን ቄሶቹ ሩጋ አሻሜ የተባለ የአውራጃ ገገር ጋ ገብተው ከሰሱን።

እኔ በማስተምርበት ወቅትም አንድ ቀን "ደህንነት ለማግኘት በመጀመሪያ ንስሃ ያስፈልጋል፤ እምነት የሚመጣው ከንስሃ በኋላ ነው።" ብዬ ሳስተምር ጳጳሱ እምነት ይቀድማል ብለውኝ ተከራክረናል። ነገር ግን እግዚአብሔር ረድቶኝ ሁሉም ለኔ አክብሮት ስለነበራቸው ምንም ችግር ሳይደርስብኝ ቀርቷል።

በዚህ መልኩ እግዚአብሔር እኔ እንዳገለግል ከመጣሁበት በቢቾ ባሻገር ሆሳዕና ከአማኞች ባሻገር እጅግ የራቁ ተደርገው በሚታዩ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች መካከል እንዳገለግል ጌታ ስለረዳኝ በቦቢቾ ቆይታዬ አስደሳች የአገልግሎት ዘመን አሳልፌያለሁ። በቢቾ ግቢ ውስጥ በነበረኝ አገልግሎትም ብዙ መልካም ሥራዎች እንዲሠሩ እግዚአብሔር የረዳኝ ሲሆን የሥራ ኃላፊዎቼም በአገልግሎቴ ይደሰቱ ነበር። በአንድ ወቅት የቅርብ አለቃዬ የሚ/ር ዳይ የበላይ የነበሩት ሚ/ር ሆጀስ የሚባሉ የኤስ.አይ.ኤም ኃላፊ በተገኙበት እኔ የሥራ ሪፖርት አቀርብ ነበር። በዚሁ ጊዜም ለባት ያህል በሚሆኑ የሥራ ኃላፊነቶቼ የተሠሩ ሥራዎችን ሪፖርት ሳቀርብ ገና አራቱን እንዳነበብኩ "እንዴ ይህ ሁሉ ሥራ እንዴት በአንድ ሰው ይሠራል? ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው።" ብለው ለሚ/ር ዳይ "በቃ ይህ ሁሉ ሥራ ይበዛበታል፤ መሥራት ያለበት ሦስት ያህል ሥራዎችን ብቻ ይሁን" ብለው በማዘዛቸው ሥራው ተቀንሶልኝ ማረፍ ችያለሁ።

## ለመጀመሪያ ጊዜ ፈራሁ

በቦቢቾ ማዕከል ያሳለፍኳቸው መልካም የአገልግሎት ዓመታት እንዳሉ ሆነው በአገልግሎቴ እና በመሪነት ኃላፊነቴ ዙሪያ ገጥሞኝ የነበረ አንድ አስፈሪ ሁኔታ ተርኬላችሁ ወደ የቦቢቾ ቆይታዬ ማጠቃለያ ሳምራ።

ቦቢቾ ገብቼ ማገልገል በጀመርኩ በጥቂት ዓመታት ውስጥ አንድ ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ ፈርቼ በማላውቀው ሁኔታ ያስፈራኝ አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር። እኔ እግዚአብሔር ጠንካራ ልብ ሰጥቶኝ ብዙም ፍርኃት አላውቅም። ወደ ሕይወቴ የመጣውን አስፈሪ ገጠመኝ እና አስጊ ሁኔታ ሁሉ ሳልደነግጥ እንደ አመጣጡ ተቀብዬ አሳልፌአለሁ። በ1962 ዓ.ም ግን በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ በጣም ፈራሁ።

በእርግጥ ያስፈራኝ እና ለወራት ስጋት ሆኖብኝ በልቤ ክብዶ የቆየው ነገር ሳጥናኤል የላከው አንዳች አስፈሪ ግኡዝ አልነበረም። በእኔ፣ በቤተሰቦቼ እና በምወዳቸው ላይ ክፉ የሚያደርስ ከኛ በላይ የገዘፈ እና የበለጠ ኃይል ያለው ጠላትም አልነበረም። ይልቁንም የፍርኃቴ መንስኤ እና የጭንቀቴ ዋና ምንጭ አንድ ከኔው ጋር በቦቢቾ በአገልጋይነት የተሰለፈ በኔው ሥር የሚሠራ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምስኪን መምህር ነበር።

ይህ ሰው ለእኔ ታላቅ ፍርኃት የፈጠረውን ነገር ያመጣውም በታላቅ ቁጣ እና በዛቻ አልነበረም። ቀስ ባለ ድምጹ ለብቻ ጠጋ ብሎ በሚረጨው የወሬ መዓት እንጂ።

ሰውየው በቢቾ በመምህርነት ተቀጥሮ እየሠራ ለካስ ሁል ጊዜ ያለ እረፍት ወሬ ከአንዱ ወደ ሌላው ሲያመላልስ ይውል ኖሯል። አንድ ቀን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላለ ነገር በቤተ ክርስቲያን ላይ ክፉ ያወራል። አንዳንድ ቀን አንዳንድ ሰዎች እንዲህና እንዲያ አደረጉ ብሎ ስማቸውን ጭቃ ሲቀባ ይውላል። አንዳንድ ቀን ደግሞ ወደ እኔ መጥቶ ሰዎች ስለኔ አወሩ የሚለውን ሀሰቱና የሚያቆሸሽ ብዙ ክፉ ነገር ይነግረኛል።

የዚህን ሰውዬ ነገር በመጀመሪያ ቀለል አድርጌ ላየው ሞከርኩ። ነገር ግን ወደ እኔም ሆነ ወደ ተለያየ ቦታ የሚያግዘው ወሬ ሲበዛ በተለይ በቤተ ክርስቲያን ላይ በቤተ ክርስቲያን መሪ አገልጋዮች ላይ የሚያወራው ክፉ ወደ እኔ ሲደርስ በጣም ያስጨንቀኝ ጀመር።

"እርሱን መሰል ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሰግስገው በቅዱሳን መካከል ክፍፍልን የሚያመጣ ወሬ እየተነዛ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ሆና የምትቀጥል ከሆነ እኔ ምን ማድረግ አለብኝ? ትልልቅ እና ገና የሚያድጉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ሲያጥላላ እና ስማቸውን ጥላሸት እየቀባ ሲያጎድፍ እኔ እንዴት መከላከል እችላለሁ? ስለ እኔ ስለ እራሴ የሚወራውን ክፉ ነገርስ እንዴት መከላከል እችላለሁ?" የሚሉ ጥያቄዎች ትልቅ የራስ ምታት ሆኑብኝ።

በእነዚህ ሃሳቦች ተወጥሬ ምን ላድርግ? እያልኩ በመጨነቅ ላይ እያለሁ የሐምሌ ወር ደርሶ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተዘጋ። ያ የጭንቀቴ ምክንያት የሆነ ሰውም ለእረፍት ወደ ትውልድ ስፍራው በመሄዱ። እኔ በቢቾ ግቢ ቀረሁ።

መስከረም ላይ ትምህርት ቤት ሲከፈትም ተመልሶ መጣ። ገና ወደ ግቢው እንደተመለሰም አንድ ክፉ ወሬ ይዞ ወደ እኔ መጥቶ መናገር ሲጀምር በፍጹም ልታገሰው አልቻልኩም። አንድ ጊዜ እንደ መብረቅ ጩኸቴን ለቀቅኩበት። "አንተ ሁል ጊዜ ቆሻሻ እንደሚሰበስብ ጥቁር ሱፍ የክፉ ወሬ ቆሻሻ እየሰበሰብክ ትመጣለህ። ከዛሬ ጀምሮ በዚህ ትምህርት ቤት መኖር ከፈለግህ አንዲት ወሬ ይዘህ ወደ እኔ እንዳትመጣ። ደግሞም አንድ ያመጣሃት ወሬ ቢኖር ላመጣሃት ወሬ ሁሉ የተናገርክበት ሰው ፊት ቀርበህ ራስህ መልስ ትሰጣለህ።" ብዬ ክፉኛ በመገሰጽ አፉን አስይዤ ላክሁት።

ሰውዬው ግን ወሬው የተለመደ ዓመል ስለሆነበት ወሬውን እኔ ጋ ባያመጣም ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን እና የተለያየ ሥራ ለሚሠሩ ሠራተኞች ያዳርስ ጀመር።

አንድ ቀን አጠቃላይ የግቢ ሠራተኞች ጸሎት በምናደርግበት ዕለት እኔ ለማስተማር እየተዘጋጀሁ እያለም እርሱ የአንደኛ ደረጃ መምህራን ሳይገቡ ቀደም ብሎ መጥቶ ቁራጭ ወረቀት ሰጠኝ። ወረቀቱንም ሳነብ "የኤለመንታሪ (የአንደኛ ደረጃ) መምህራን መንፈሳዊ ሕይወት ጥሩ አይደለም፤ ስለዚህ ልትገስጻቸው ይገባል።" ይል ነበር። እኔም

የሰጠኝን ወረቀት እርሱ ቁጭ ባለበት አነበብኩት እና ወዲያው ሌላ ማስታወሻ ጽፌ ሰጠሁት። በጻፍኩት ማስታወሻ ላይም "አጥፊውን ለብቻ እኔና አንተ አብረን ሆነን እንመክራለን እንጂ ሁሉንም በአንድ ላይ መገሰጽ ተገቢ አይደለም።" ብዬ ነበር።

ለካስ እርሱ ወደ ፕሮግራሙ ከመግባታችን በፊት ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራኑ ስለ እኔ መጥፎ መጥፎ ነገር እና እኔ እነርሱን እንደምጠላ ነግሯቸው ነበር። እነርሱም በዚህ አዝነው በኔ ዙሪያ በቁጣ ተሞልተው ነበር ወደ ፕሮግራሙ የገቡት። አንድ ነገር ብናገራቸውም መልስ ሊሰጡኝ ተዘጋጅተው ነበር። ይሁንና እግዚአብሔር በዚያ ዕለት ጥበብ ስለ ሰጠኝ ምንም ሳልናገራቸው ቀረሁ። በዚህ ጊዜ ያ ሰው በተቀመጠበት ላብ በላብ ሆኖ የትምህርቱ እና የጸሎቱ ጊዜ አለቀ። ሰው ሁሉ ከሄደ በኋላም ወደ እኔ መጥቶ ወረቀቱን መልስልኝ አለኝ። እኔም "አይ ክፉ ነገር ያየህበትን ያጠፋ ሰው አምጥተህ አብረን እንመክራለን እንጂ እንዲሁ አንተውም" አልኩት።

እርሱም በስጋት ሲያስብ ቆየ እና "በቃ እኔ እመክረዋለሁ፤ ወረቀቱን ግን ስጠኝ" አለኝ። እኔም እግዚአብሔር ማስተዋል ሰጥቶኝ በአቋሜ ጸናሁ። እርሱ ግን በነገሩ በጣም ስጋት ስለገባው "በቃ እሺ አጥፍቻለሁ፤ ይቅርታ አድርግልኝ እና ወረቀቱን ስጠኝ" አለኝ። እኔም በጄ አላልኩትም። ከዚያ ከክፍሉ ወጥቼ ወደ ቤቴ መሄድ ጀመርኩ። በዚህ የትምህርት ቤቱ ሰንደቅ ዓላማ መስቀያ አካባቢ ስደርስ ለሦስተኛ ጊዜ አስተዛዝኖ ወረቀቱን ለመነኝ። እኔም "ያጠፋውን ሰው ሳንመክር አልሰጥህም" አልኩት።

በመጨረሻ እኔ ወደ ቤቴ ስቃረብ በዝምታ ሲከተለኝ ቆይቶ "በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል" ብሎ እግሬ ላይ ወደቀ። እኔም "መምክርህን ማረጋገጥ ስለምፈልግ ያጠፋውን ሰው ስም ንገረኝ እና እሰጥሃለሁ።" አልኩት። የሰውየውን ስም ሲነግረኝም እኔ የልቤ እንደሆነ አድርጌ የምቆጥረው ለግቢያችን በጣም ጠቃሚ እና አስፈላጊ አስተማሪ ሆኖ አገኘሁት። ቢሆንም መምክርህን እጠይቃለሁ። ብዬ ወረቀቱን ሰጠሁት እና ተለያየን።

በኋላም ለ15 ቀናት ያህል መምከር አለመምከሩን ስጠይቀው ቆየሁ። በጠየቅሁት ቁጥር ሳይመክር ቆይቶ ቀጠሮ ይሰጣል። በመጨረሻ ያለው ሰው ጋ ሄጄ "መጥቶ መከረህ ወይ?" ብዬ ጠየቅሁት። በዚህ ጊዜ ሰውዬው በድንጋጤ ጮኸ። ከዚያም በዚያ ዕለት የሆነውን ነገር ነገረኝ። "በዚያ ዕለት ሁላችንም አንተ እኛን ትናገራለህ ብለን ተዘጋጅተን ተቆጥተንብህ ነበር የገባነው። ነገር ግን ምንም ሳትናገር ወጣህ።" አለኝና በጣም አዘነ።

እኔም ወዲያው "ስለ ሰውየው ምን እናድርግ?" አልኩት። በእርሱ ላይ ተነስቼ እርምጃ ብወስድ ሰዎች የእርሱን ጥፋት እና ክፉ ማንነት አያዩም። ዝም ብለው ኬዳሞ እገሌን አባረረው ነው የሚሉኝ። ስለሆነም በቃ እንተወው ተባብለን ተስማማን። ያ አስተማሪም በነገሩ እና በሰውዬው ክፋት ተገርሞ "እንደነዚህ ያሉ ሰዎች መንግስተ

ለማይ የሚገቡ ከሆነ እኔ ፈጽሞ አልጠየቅም።" አለ። ያ ሰው ከዚህ አጋጣሚ በኋላ እስከ ተለያየንበት ጊዜ ድረስ ግን አፉን ዘግቶ ኖረ። ያኔ በክፍል ውስጥ ገስጾ እንዳለኝ አንድ ቃል ተናግሬ ቢሆን ኖሮ የቦቢች ግቢ የጸብ እና የነገር ሜዳ በሆነ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበብ ሰጥቶኝ ክፉውን አመለጥኩት።

## የቦቢች ቆይታ ማብቂያ

የቦቢች ቆይታችን መጨረሻ አካባቢም ከውጪ እና ከውስጥ ከሚመጡ የአገልግሎት ጥሪዎች የተነሳ ወደ በርካታ አካባቢዎች ያለ ዕረፍት እጓዝ ስለነበር ከተፈጠረው ከፍተኛ ጫና በመፈጠሩ ኃይለኛ ራስ ምታት እየያዘኝ እሰቃይ ጀመር። አንዳንድ ጊዜ ጭንቅላቴ ላይ እንደ ድንጋይ የሚንከባለል ነገር እየተሰማኝ አካላቴን ሁሉ እየወጋኝ እታመም ስለ ነበር ማሰብ ሁሉ እያቃተኝ ተቸገርኩ።

በ1964 ዓ.ም ጥር ወር ላይም በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ እንኳ አገለግል ነበርና ወደ ወላይታ ለአገልግሎት ሄጄ ከዚያም ምንም ሳላርፍ ወደ ዋካ ተሻገርኩ፤ አሁንም ምንም ሳላርፍ በአውሮፕላን ወደ ኮንታ ኮይሻ እና በረዳ በመጓዝ ካለ እረፍት ለአንድ ወር ያህል እየተጓጓዝኩ አገለገልኩ። ልክ ኮንታ ኮይሻ ስደርስም ድካሜ ተባባሰና ራሴን በኃይል አዙሮኝ ወደ ራስን መሳት ተቃረብኩ። በዚህ ጊዜ የከፋ ነገር እንዳይገጥመኝ ሰግቼ "ጌታ ሆይ ስምህን አክብር" እያልኩ ለግማሽ ሰዓት ያህል ስጸልይ ቆይቼ ወደ አእምሮዬ ተመለስኩ። እንደምንም የቆይታ ጊዜዬን ጨርሼም ወደ ቦቢች ተመለስኩ።

ነገር ግን ሕመሙ ከገቢ መልስም ስላልለቀቀኝ ቤቴ እንደገባሁ ታምሜ አልጋ ያዝኩና በላዬ ላይ በር ተዘግቶብኝ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ባለቤቴ እየሰጠችን ለአንድ ወር ያህል ተኛሁ። አንድ ቀንም ወንጌላዊ ፍቅሬ መኮሮ የሚባል አገልጋይና አቶ ሀሪሶ የሚባሉ ሽማግሌ ወደ ቤት መጥተው ባለቤቴን ፈቃድ ጠይቀው በመግባት በኔ ላይ እጅ ጭነው ጸለዩልኝ። በዚህ ጊዜ ሁሉ እኔ እንቅልፍ ወስዶኝ ተኝቼ ነበር። ቆይቼ ስነቃ ግን ሕመሙ ከላዬ ላይ ተነስቶ ወደ ሙሉ ጤንነቴ ተመልሼ ነበር።

ከዚህ በኋላም እንደገና አገልግሎት መስጠቴን ቀጥዬ በክረምት ወራት ተከታታይ ትምህርቶች በልዩ ልዩ ቦታዎች ለማስተማር ወደ አዲስ አበባ እመላለስ ጀመር።

የቦቢች የአገልግሎት ጊዜዬም ሰባት የፍጽምና ዓመታት እየሞላ ሄዶ ከሆሳእና ምድር የምለያይበት ጊዜ ደረሰ።

# ምዕራፍ ፲፯

# ከቦቢቾ ወደ አዲስ አበባ ማሰብ ...

## ‹‹ተሻገር እና እርዳን...››

*ወንጌላዊ ኬዳሞ በገጠራቱ ኢትዮጵያ ተወልዶ በዚያው ያደገ ሲሆን በተለያዩ የቀድሞ የአገሪቱ ገጠር ቀመስ እንደ ዲላ፣ ሻሸመኔ፣ ሆሳዕና እና ዱራሜ ያሉ ከተሞች በመዘዋወር አገልግሏል። ሆኖም በእነዚህ ግዜያቱም ቢሆን ራሱን እንደ አንድ የገጠር የወንጌል አገልጋይ ይቆጥር ነበር። ከዚህ ቀደም ለግል ጉዳይ ሻሾን ነዋሪ በነበረበት ጊዜ አዲስ አበባን ሄዶ ያያት ቢሆንም ከአገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ወደ እዚህች ከተማ ሄዶ የመስንበት እድል ያጋጠመው ግን በ1961 ዓ.ም የክረምት ወራት ነበር። በዚህ ጊዜ ኬዳሞ በቂራ አካባቢ በሚገኘው የጂ.ሲ.ኤ (ገርልስ ክርስቲያን አካዳሚ) የሚሲዮን ማዕከል ውስጥ ከመላ አገሪቱ ለተሰባሰቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መምህራን የሚሰጥ የአንድ ወር ሥልጠና ለመካፈል በመጣበት ወቅት ከመሰል መምህራን ጋር ለመገናኘት በቃ።*

*የአገሪቱ ርዕሰ መዲናና የበርካታ ልዩ ልዩ ተቋማት መገኛ የሆነችው አዲስ አበባ ያኔም ቢሆን ከሌሎች የአገሪቱ ከተሞች ለሚመጡ ሁሉ አስደናቂ፣ የሆነች ዘመናዊ እና የደራች ከተማ ነበረች። ኬዳሞም ወደ አዲስ አበባ ለሥልጠና ሲያመራ በከተማይቱ ከከተሙ ምሁራን እና የበለጠ እውቀት ያላቸው የወንጌል አገልጋዮች ለመማር አስቦ ነበር። ይሁንና በጂ.ሲ.ኤ ሥልጠናውን እየተከታተለ በነበረበት በአንዱ እሁድ በማዕከሉ ባለው የሰንበት አምልኮ ላይ መልእክት እንዲያቀርብ ተጋበዘ። 'እኔ የገጠር ከተማ አገልጋይ ነኝ' ብሎ የሚያስበው ወንጌላዊ ወንጌልን በመላ አገሪቱ ይዞ ለመዞር እንደተጠራ ስለሚያምን ይህንን የአገልግሎት ዕድል በሚገባ ሊጠቀምበት ወደደ። አስቀድሞ እንደ ተሰጠው ጸጋም በ1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 2-16 ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ መሠረት አድርጎ "እውነተኛ የወንጌል አገልጋይ ምን ዓይነት ነው?' በሚል ርዕስ ሰበከ።*

*በዚህ ጊዜ የቦቢቾው አገልጋይ ያቀረበውን የወንጌል ስብከት የሰሙ እና የተባረኩ ወገኖች ስለ ወንጌላዊው ድንቅ መልእክት አቅራቢነት ለሌሎች ተናገሩ። ይህ ዜና ወደ ያኔዋ አንጋፋ የአዲስ አበባ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጆሮም ደረሰ። የጌጃ መሠረተ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሳይውሉ ሳያድሩ ወንጌላዊው በቤተ*

ክርስቲያኒቱ አንድ ሰንበት እንዲያገለግል ጋበዙት። ወንጌላዊው በዚያው የሥልጠና ቆይታው ጊዜ በጌጃ ቃለ ሕይወት የሰንበት አምልኮ ላይ ሊሰብክ ተዘጋጅቶ ወደ እዚያው አመራ።

ኬዳሞ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መድረክ ከዚያ በኋላም ሆነ ከዚያ በፊት ማንም ከእርሱ በላይ በተደጋጋሚ ያልቆመበትና የማይቆምበት የበርካታ አስርት ዓመታት የአገልግሎት መድረኩ እንደሚሆን ባያውቅም በዚያች የ1961 ዓ.ም አንድ የክረምት ሰንበት የመጀመሪያ አገልግሎቱን በስፍራው ለነበሩት ጥቂት ምዕመናን አበረከተ።

በዚህ ዕለት ወንጌላዊው በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 12-17 ባለው ሃሳብ ላይ መሠረት አድርጎ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሦስት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ እየገለጸ ሰበከ። ሐዋርያው ዮሐንስ በተጠቀሰው ክፍል እንደሚናገረው እነዚህ ሦስት ዓይነት ሰዎች የመጀመሪያዎቹ ሕፃናት ሲሆኑ ጎልማሶች በሰውነት ያደጉ ቢሆኑም በመንፈሳዊ ማንነት ሕፃናት ሊሆኑ እንደሚችሉ ገለጸ። አንዳንዶች ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እያደጉ የሚሄዱ እና ያደጉ ጎልማሶች ናቸው። በመጨረሻ ያሉት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሆኑ የቆዩ ክርስቲያኖች ናቸው። ስለሆነም እነዚህ ሦስቱንም ቤተ ክርስቲያን እና አገልጋዮቿ እንደየ ሁኔታቸው አስፈላጊውን ድጋፍ እየሰጡና ችግራቸውን እያወቁ ልትይዛቸው እንደሚገባ ተናገረ። ሕፃናት የተለያየ የምግብ አምሮት እንደሚያስቸግራቸው፤ ጎልማሶችም በሚያውቁትና በተማሩት መሠረት መኖር እንዳለባቸው፤ እንዲሁም አባቶች የሆኑት ከዚህ ቀደም በተሠራውና ባላቸው ገንዘብ የመከበር ፍላጎት እንደሚኖራቸው ካስረዳ በኋላ ቁጥር 17 ላይ በተሰጠው የማጠቃለያ ሃሳብ መሠረት ሁሉም ለቃሉ መታዘዝ እንደሚገባቸው ገለጸ። በመጨረሻም የእግዚአብሔር ቃል መሪያቸው መሆን እንዳለበት በማስገንዘብ ስብከቱን አጠቃለለ።

ከዚህች ዕለት በኋላ ኬዳሞ የጌጃ መሠረተ ሕይወት ቤተኛ ሆነ። ጠንካሮቹ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚያዘጋጁት ልዩ ፕሮግራሞች ሁሉ ኬዳሞን መጋበዝ ተቀዳሚ ተግባራቸው ሆነ። የፋሲካ እና የገና ኮንፍራንሶችና የክረምት የትምህርት ፕሮግራሞች ኬዳሞ በዋናነት የሚያገለግልባቸው ጊዜያት ነበሩ። ከዚህም አልፈው በልዩ ልዩ የመንግስት ኃላፊነት በመሥራት አገራቸውን በማገልገል ላይ ያሉት የጌጃ መሪዎች ኬዳሞን የጌጃ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ አድርጎ መያዝ ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚያሳድግ እርምጃ እንደሆነ በማመን ወንጌላዊው ወደ አዲስ አበባ ጠቅልሎ በመምጣት ሙሉ ጊዜውን ለጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እንዲሰጥ ጥያቄ ያቀርቡ ጀመር።

ኬዳሞ ከ1961 ዓ.ም ክረምት የጂ.ሲ.ኤ ቆይታ በኋላ በየጊዜው አዲስ አበባ እየተመላለሰ ያገለግል ገባ። ከ1962 እስከ 1964 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያንን በእንግድነት እየተጋበዙ ሲያገለግል ቆየ። በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ኬዳሞ ቋሚ አገልጋዩዋ እንዲሆን ደጋግማ ጥሪ ታቀርብለት ነበር። ይሁንና ኬዳሞ

በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ማገልገል የሚቻል መስሎ አልታየውም ነበር።

ከእነዚሁ በወንጌላዊው ልብ ከነበሩ ምክንያቶች ዋነኛው ዘናጮቹ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በሙሉ በኬዳም እይታ በጣም የተማሩ ሰዎች ይመስሉት ነበር። ስለሆነም "ለእነዚህ የከተማ ሰዎች አገልግሎት እንደ እኔ ያለ የገጠር ወንጌላዊ ሆኖ ብዙ ዘመን ያሳለፈ ሰው ያለው እውቀት በጣም ያንሳል።" ብሎ ያስብ ነበር። ከዚህም ሌላ ኬዳም በጣም አስፈላጊ ሆኖ እያገለገለ ያለበት የተረጋጋ ቦታ እና ብዙ ሥራዎች በቦቢቾ ነበሩት። እንዲሁም ደግሞ ኬዳም እና ባለቤቱ በቦቢቾ ማዕከል ከሰባት ልጆቻቸው ጋር የሚኖሩ ሲሆን ይህ ሁሉ ቤተሰብ በዚያ ዘመን ካሉት የኢትዮጵያ ከተሞች ሁሉ ኑሮ ውድ በሆነባት አዲስ አበባ መሰባሰቡ ሌላው ነገሩን የማይሆን ያደረገ ጉዳይ ነበር።

ወንጌላዊ ኬዳም እና ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በዚህ መልኩ ሲሳሳቡ አራት ዓመታት አልፈው አምስተኛው መጣ። በ1965 ዓ.ም የገና በዓል ወቅትም ኬዳም እንደገና ለክርስቶስ ልደት በዓል መታሰቢያ በተዘጋጀ ኮንፍራንስ ላይ እንዲያገለግል ተጋብዞ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ኮንፍራንስ ላይ ካገለገለ በኋላ የተለመደው የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ጥያቄ ተከተለ። በዚያ ዘመን ከነበሩት የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች አንዱ የሆኑት ጨዋታ አዋቂው አቶ ላቀው ተሰማ እና ሌሎችም በጋራ ሆነው በኮንፍራንሱ ማብቂያ ላይ በነበረው እሁድ ምሽት ላይ "ና እና በቋሚነት አገልግለን" የሚል ጥያቄያቸውን እያዋዙ አቀረቡ። ኬዳምም የተለመደውን "እኔ ለተማረው የአዲስ አበባ ሕዝብ የሚመጥን እውቀት የለኝም። ... ወደ እዚህ ብመጣ በቦቢቾ ያለኝ አገልግሎት እንዴት ይሆናል?" የሚለውንና ሌሎችንም በርካታ ምክንያቶችን ዘርዝሮ አይሆንም የሚል ምላሽ ሰጠ።

ከሁሉም በላይ እስከ ዛሬ ድረስ በብዙ አቅጣጫ ስትጓዝ የነበረችው የወንጌላዊው ሕይወት አንድ የተለማመደችው የሕይወት መርህ ነበራት። ወደ የትም ቢሆን እንደ የእግዚአብሔር ሰው ዳዊት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቆ መውጣት! ስለሆነም "የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ስላለብኝ የእርስዑን ፈቃድ ሳላውቅ አልመጣም።" የሚለው ምላሹ የጌጃንም መሪዎች ዝም የሚያሰኝ ነበር።

በዚያው ዕለት ማታም ወንጌላዊው ቀደም ሲል ወደ ሚያውቃቸው ወዳጁ እና በአዲስ አበባ ዘነበ ወርቅ አካባቢ ኗሪ ወደ ሆኑት አቶ በራሳ ቤት ለአዳር ሄደ። በማግስቱ ሰኞ ማለዳም ወንጌላዊው እንደ ሁል ጊዜ ልማዱ ወፎች ዝማሬያቸውን ሳያሰሙ ተሽቀዳድሞ ለጸሎት በመነሳት የተለመደውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱን አካሄደ። በዚያ ማለዳ "እግዚአብሔርን መታዘዝ" በሚል ርእስ ሥር የተለያዩ ጥቅሶችን ሲያነብም ቆየ። በዘፍጥረት 6:21 ላይ "ኖህ እግዚአብሔርን ታዘዘ ... እንዲሁም እግዚአብሔር አብርሃምን ከዘርህ ከነገድህ ተለይተህ ውጣ" እንዳለውና በ2ኛ ነገስት ምዕራፍ 6 ላይ እግዚአብሔር ኤልያስን "ወደ ኮራት ፈፋ ወዳለው ወንዝ ውረድ እኔ በቁራ እመግብሃለሁ" እንዳለው አነበበ። በዚሁ ወቅትም ካነበባቸው ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ምን እንደሚማር ማሰላሰል ጀመረ። ወዲያውኑም መንፈስ ቅዱስ

በግልጽ "አንተ ታዲያ ለምን በር ትዘጋለህ?" ብሎ ስለ ተናገረው ወዲያው "እሺ ያንተ ፈቃድ ይሁን።" ብሎ ለመታዘዝ ወሰነ።

ወንጌላዊ ኬዳሞ በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር መክሮ የተስማማው ጥር 1 ቀን 1965 ዓ.ም ነበር። የዚያን ዕለትም ለአራት ዓመታት በእምቢታ ሲመልስላቸው ከነበሩት የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ወደ አንዱ አመራ። በጊዜው ኬዳሞ ያገኛቸው የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪ አቶ ላቀው ተሰማ ነበሩ። በቀልድና ጨዋታ አዋቂነታቸው የሚታወቁት አቶ ላቀውም ኬዳሞን በደስታ ተቀብለው አነጋገሩት።

ኬዳሞ ከጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አስተዋይ መሪዎች አንዱ ለነበሩት ለአቶ ላቀው ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር መክሮ የደረሰበትን ውሳኔ አጫወታቸው። ከዚያች ጥር አንድ ቀን ጀምሮም እስከ ሰኔ ባሉት አምስት ወራት ጌጃዎች በጸሎት እንዲቆዩ እና እግዚአብሔር በወንጌላዊ ኬዳሞ ቦታ ተተክቶ በቦቢቾ የሚያገለግል ሰው እንዲያዘጋጅ፤ ኬዳሞ ለሰባት ዓመታት ያህል ያገለገለበት ኤስ. አይ. ኤም ኃላፊዎች እንዲፈቅዱ እና ኬዳሞ ራሱን ለወንጌል አገልግሎት ከለየበት ጊዜ አንስቶ ከሃያ ዓመታት በላይ በልዩ ልዩ አቅጣጫ ሲያሰማራው የነበረው የከምባታ እና ሃዲያ አውራጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም እንዲፈቅድ እንዲጸልዩ ጥያቄ አቀረበ።

ኬዳሞ በዚህ ጉዳይ እየጸለየ እና ማድረግ ያለበትን እያደረገ ሲቆይ እንዲሁም አዲስ የደረሰበትን ውሳኔ ለባለቤቱ ሊያሳውቅ እና ሊመክር የአዲስ አበባ ቆይታ ጊዜውን ጨርሶ ወደ ቦቢቾ ተመለሰ። ወራቱም በፍጥነት ነጎዱ። በዚህ መሐልም አንዳንድ የኬዳሞን ውሳኔ የሰሙ አዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑ ወዳጆቹ አዲስ አበባ ውስጥ ኑሮ ውድ መሆኑን በማሰብ "አዲስ አበባ ይህን ሁሉ ቤተሰብ ይዘህ ከመጣህ ለልጆችህ ሽሮ ጫማ እንኳን መግዛት አትችልም።" እያሉ ስጋታቸውን ገለጹ። ከዚህም ባሻገር ኬዳሞ እና ወ/ሮ ታደለች ቦቢቾ እያሉ ከነበራቸው ከባድ አገልግሎት አንዱ ከመላው የከምባታ እና ሃዲያ ምድር ዙሪያ ገባ የሚመጡ እንግዶችን በቤታቸው ተቀብለው ማስተናገድ ነበር። ይህንኑ የሚያውቁ የኬዳሞ ወዳጆችም "በሆሳዕና ቆይታህ በአገር ደረጃ እውቅና ያገኘህ የሁሉ አገር ሕዝብ አገልጋይ ሆነሃል። አሁን ከቦቢቾ በባሰ የመላ አገሪቱ ሕዝብ ለልዩ ልዩ የግል ጉዳዮቹ ወደ አዲስ አበባ ይመጣል። አንተ ደግሞ እንግዳ መቀበል ትወዳለህ። ታዲያ አንተ በአዲስ አበባ ኑሮ እንዴት ብለህ የመጣውን እንግዳ ሁሉ እየተቀበልክ ልትኖር ነው?" አሉት።

በዚህ ጊዜ ኬዳሞ "እኔ እንግዲህ የጠራኝ እግዚአብሔር ነው ለኔም ሆነ ለልጆቼ ኃላፊነቱን የሚወስደው ራሱ ነው።" ሲል መልስ ሰጠ። እንግዳ ከመቀበል አንጻርም "እኔ በማገለግልበት ቦታ ሃያ ሰዎች ቢኖሩ ከእነርሱ መኃል ሁለት ሰው መርጬ ወደ ቤቴ አልወስድም። ነገር ግን በእንግድነት የመጣ ማንንም በቤቴ እቀበላለሁ። የዚህንም ኃላፊነት እግዚአብሔር ይወስዳል።" ብሎ ምላሽ ሰጠ።

*በእርግጥ ኬዳሞ ራሱ አውጥቶ ባይናገረውም 'የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሁሉ የተማሩ ናቸው' ከሚል ሃሳብ ተነስቶ "ጌጃ የምሰጠው አገልግሎት ላይሳካልኝ ይችላል። አዲስ አበባ ረጅም ዘመን መቆየት አልችልም። አንድ ቀን የጌጃ መሪዎች ራሳቸው ወደ መጣሁበት ይመልሱኛል" ብሎ ያስብም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር የተናገረው አይቀርም እና የኬዳሞ ጉዞ እውን ሊሆን ቀናት ይቃረቡ ጀመር። ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም ጥያቄዋን ሥርዓት ለማስያዝ ለከምባታ እና ሃዲያ አውራጃ ደብዳቤ ጽፋ አቀረበች። የከምባታ እና ሃዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም ጥያቄውን ተቀብላ ወንጌላዊውን ልክ አውራጃው ራሱ ለወንጌል አገልግሎት እንደሚልከው አገልጋይ ሾኔ ላይ በተደረገ ትልቅ ጉባኤ የአውራጃው አንጋፋ መሪዎች እነ አባ ጎሌ በተገኙበት ጉባኤው በሙሉ ቆሞ ጸልዮለት ኬዳሞን ወደ ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሸኙት። የኤስ. አይ. ኤም (መሪዎችም ምንም እንኳን በኋላ የአገልግሎት ካሳ ባለመክፈል ቅር ቢያሰኙትም) የወንጌላዊውን ጥያቄ ተቀብለው ሊለቁት ፈቃደኛ ሆኑ። ኬዳሞም በእርሱ ቦታ ተተክቶ እንዲያገለግል ወንጌላዊ ወንድሙ ጂካሞን ጠቁሞ እርሱ ከባቢቾ የኤስ. አይ. ኤም ማዕከል ተሰናበተ።*

*'ወደ አዲስ አበባ ሄጄ ቆይታዬ ረዝሞ ቀሪ ዘመኔን ሁሉ ማሳልፈው እዚያው ይሆናል።' ብሎ ሳያስብም አነስተኛዋ የአዲስ አበባ ከተማ ቤተ ክርስቲያን የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሆኖ ሊያገለግል ጓዙን ጠቅልሎ ከወገኖቹ እና ከሥጋ ዘመዶቹ ተለይቶ ወጣ። አንድ ቀን እመለስ ይሆናል ብለው እያሰበ በመጣባት በአዲስ አበባም ከአራት አስርት ዓመታት በላይ ብዙ አስደናቂ ምዕራፎችን እየተሻገረ ሊኖር እና ከትንሿ ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተነስቶ በመላ አገሪቱ ብሎም በዓለም ዙሪያ ሁሉ እየተዘዋወረ የሚያገለግል አገልጋይ እንደሚሆን አላወቀም። በጊዜውም የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ልትከፍለው የወሰነችው 250 ብር የወር ደመወዝ የእርሱን ቁጥሩ የበዛ ቤተሰብ በአዲስ አበባ እንዴት እንደሚያኖር ባያውቅም የጠራውን እግዚአብሔርን ታምኖ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ወሰነ።*

## ደማቁ ሽኝት

*ወንጌላዊ ኬዳሞ ወደ አዲስ አበባ መሠረተ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተዛውሮ በወንጌላዊነት እንዲያገለግል የቀረበለት ጥሪ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳለበት አምኖ ሊሄድ ወስኖ መዘገጃጀት ጀምሯል። ወንጌላዊው በባቢቾ ማዕከል ለ7 ዓመታት ያህል በሰጠው አገልግሎት የተባረኩ እና ብዙ መልካም ጊዜያትን አብረው ያሳለፉ ወገኖች በመለየቱ የተሰማቸውን ኃዘን እና በአንጻሩ ደግሞ የመልካም ምኞት መግለጫቸውን እያሰሙ አንዳንዶች በተናጠል አንዳንዶችም በኅብረት እየሆኑ ወንጌላዊውንና ቤተሰቡን ተሰናበቱ።*

*ወንጌላዊው በትጋት ያገለገለበት የኤስ.አይ.ኤም ተቋም ዝውውሩን ፈቅዶ የተስማማ ቢሆንም አስፈላጊውን ሽኝት ለማድረግ ዳተኛ መሆኑ ወንጌላዊውን አሳዝኗል። ኤስ.አይ.ኤም በዚህ ጊዜ ሳያደርገው የቆየውን የአገልግሎት ክፍያ በወንጌላዊው የኋለኛ*

ዘመን ከብዙ ዓመታት በኋላ እንደተፈጸመ ወንጌላዊው አስታውሶ በጊዜው ይተርከልናል።

ኬዳሞ ጌታን ካገኘበት አፍላ የወጣትነት ዘመኑ ጀምሮ የወጣት አገልጋይነት የሕይወት እፍታውን ጨምሮ እስከ ጎልማሳነቱ ድረስ አብዛኛውን ጊዜውን እየተዘዋወረ በማገልገል ያሳለፈባትን የከምባታ እና ሃዲያ አውራጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን የሚለይበት ጊዜ እውን ሆኗል። እነዚህ ከሁለት አሥርት ዓመታት የዘለሉ የአገልግሎት ዘመናት ወንጌላዊው ሙሉ በሙሉ የዚህ አውራጃ አገልጋይ ሆኖ የኖረ ሲሆን ከአውራጃው ውጪ ወዳለው ወደ ጌዲኦ ምድር በወንጌላዊነት ሲላክም እንኳን በዚሁ አውራጃ አሰማሪነት ነበር የሄደው። ወደ ኤስ አይ ኤም የበቢቾ ማዕከል ሲዛወርም የአውራጃው መሪዎች ከተቋሙ ጋር አብረው ከመከሩ በኋላ ወንጌላዊው በጋራ ኃላፊነቱን እንዲቀበል ጠይቀው እንደነበር ይታወሳል። በዚህ ጊዜም ወንጌላዊው በአዲስ አበባ ጉዞው ላይ ይሁንታቸውን እንዲሰጡ እና በጸሎት እንዲሸኙት ለአውራጃው ዋና መሪዎች ለእነ አባ ጎሌ ጥያቄ አቀረበ። የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቀደምት አባቶች የሆኑት አባ ጎሌ እና አጋሮቻቸውም ጥሪውን አክብረው መጥተው ወንጌላዊውን በጸሎት ለጌታ አሳልፈው ሰጡ።

ከዚህ ሁሉ የሽኝት ሥነ ሥርዓት በላይ የወንጌላዊውን ልብ በትዝታ ዛሬም ድረስ ጨምድዶ የያዘ አንድ የሽኝት አጋጣሚ ተከናውኖ ነበር።

ኬዳሞ ለአራት ዓመታት ያህል ከበቢቾ በመነሳት በየእሁዱ ከሰዓት እየተመላለሰ ለአራት ሰዓት ያህል ያስተምራቸው የነበሩ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች እና ሌሎች ተገልጋዮች በጋራ ሆነው የሽኝት ሥነ ሥርዓት አካሄዱ። በዚሁ ጊዜም ትምህርቱን አስቀድሞ በስህተት ፈላጊነት እና አንዳች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምትቃወመው ትምህርት ይቀርብ እንደሆነ ለማየት የመጡ በርካታ የአካባቢው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባላት በሽኝቱ ላይ ተገኝተው ነበር። ብዙዎቹም ተራ በተራ እየተነሱ ስለ ወንጌላዊው እና ስላስተማረው ትምህርት ሃሳባቸውን ሰጡ።


አንድ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እና የአካባቢውን ሲኖዶስ መንፈሳዊ ሥራዎችን በበላይነት የሚመራ ሰው ተነስቶ "ሆሳዕና ውስጥ ማንም ሳይነካው የሚኖር ያልሞተ ዘንዶ ነበረ። አሁን ግን የዚያ ዘንዶ ጭንቅላት በወንጌላዊ ኬዳሞ ትምህርት ተመትቷል። ነገር ግን ዘንዶው ሳይሞት ኬዳሞ በመሄዱ በጣም አዝናለሁ።" ብሎ የምሩን ተንሰቅስቆ አለቀሰ።

ትምህርቱን ሲከታተል የኖረ አቶ በላይ የሚባል የፖስታ ቤት ሹም ደግሞ "እኛ መጽሐፍ ቅዱስ በእጃችን ላይ ለብዙ ዓመታት አለ። ነገር ግን የተዘጋ መጽሐፍ ነበር። አሁን በአቶ ኬዳሞ እየተከፈተልን ነበር። ነገር ግን ምን ዋጋ አለው? በደንብ ሳይገባን ትቶ በመሄዱ በጣም አዝናለሁ።" ብሎ ቅሬታውን ገለጸ። በሆሳዕና ከተማ በሚኖሩ ብዙ ሰዎች ስለ ወንጌላዊው በርካታ ነገሮች ተነገሩ። አጠቃላይ ሥነ ሥርዓቱም በደንብ ታስቦበት የተዘጋጀ ትልቅ የሽኝት በዓል ነበር። በዚሁ ሽኝት ላይም በሌላ ስፍራ


*እምብዛም ባልተለመደ ሁኔታ ከዚህ ቀደም የኬዳሞን ትምህርት እየተከታተሉ ሲሞግቱ የነበሩት ጳጳስ በስፍራው በክብር እንግድነት ተገኝተው ነበር። እኚሁ አባትም በመጨረሻ "መንፈሳዊ አገልጋይ ማለት ይህ ነው።" ብለው ስለ ኬዳሞ መልካም ምስክርነት ሰጡ። ወንጌላዊውም እነዚህን ሁሉ መልካም ትዝታዎች ተሸክሞ የፖለቲካ ትኩሳቷ እየጨመረ ወደ ነበረችው አዲስ አበባ አመራ።*




የኬዳሞ የትውልድ አገር ሻሾጎ



የኬዳሞ የትውልድ አገር መንደር (የመኖሪያ ጎጆዎች)



ኬዳሞ እና መንፈሳዊ አባታቸው አቶ ሳህሌ ጀፌ በጉልምስና እድሜያቸው



ኬዳሞ እና የመጀመሪያው ተማሪያቸው ከዚያም
የሻሾጎን ምድር የወንጌል አደራ ያስረከቧቸው
ወንጌላዊ አቡዬ ቲርካሶ በወጣትነታቸው




ኬዳሞ እና ወ/ዊ አቡዬ በሽምግልና ዘመናቸው




ወ/ዊ አቡዬ እና ኬዳሞ ያደነቁት በቦቢቾ ግቢ
የሚገኘው የያኔው የሚስ ማክለክ ቤት




በኬዳሞ ተተክሎ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት
ቤትንት ያደገው የኡርበጫ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት




ኬዳሞ እና የጌዴኦ ምድር የአገልግሎት አጋራቸው
ሚ/ር አልበርት ብራንት በካናዳ ተገናኝተው




ሚ/ር አልበርት ብራንት




ኬዳሞ ጎብኝተው ሃዘናቸውን የገለጹበት
የወዳጃቸው ሚ/ር አልበርት ብራንት መቃብር




"አስተምረው ለፍሬ ያበቁትን ማስመረቅ
እንዴት ደስ ያሰኛል"




"ጌታ በኩየራ አገናኘን እስከ እዚህ
ዓመት ድረስም ለ60 ዓመታት ጓደኞሞች ሆንን"
ከዶ/ር ሙላቱ ባፋ ጋር




እኔና ሚ/ር ዳይ ከተማሪዎቻችን ጋር በቦቢቾ



ከግቢው ሠራተኞች ጋር በቦቢቾ



ከሚ/ር ዳይ እና ባለቤታቸው ጋር
በአሜሪካ እንደተገናኘን



በናዝሬት የአቢያተ ክርስቲያናት ኅብረት
መሪዎች ጉባዔን በመካፈል ላይ



ወደ ጉልምስና በማዝገም ላይ ያለው ወንጌላዊ



በጨቦ ከነበሩ አገልጋይ ወዳጆቼ ጋር

*በዚህ ክፍል ሊገቡ የሚገባቸው ተጨማሪ ታሪካዊ ፎቶዎች ከወንጌላዊ ኬዳሞ ባለቤት ህመም ጋር በተያያዘ በተደረጉ ጉዞዎች ወቅት በመጥፋታቸው ማካተት አልተቻለም፡፡*